# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 078 ኅዳር 18 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



pepsi


# "በታዳሽ የኃይል ምንጮች ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት እየተሠራ ነው"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)




**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ታዳሽ የኃይል ምንጮችን እምቅ አቅም በመጠቀም ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢንዱስትሪ ልማት 20ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን እምቅ አቅም ተጠቅሞ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን አጽንዖት ሰጥተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም፤ የኢንዱስትሪ መስፋፋት በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦችን ከድህነት አረንቋ ሊያወጣ እንደሚችል ተናግረዋል፡፡

በሀገራዊ የኢነርጂ ፖሊሲና በተለያዩ ዘርፎች በሚዘረጋው የኢነርጂ ውጤታማነት ስትራቴጂ መንግሥት ከንፁሕ የኃይል ምንጭ የሚገኘውን የኤሌክትሪክ ኃይል በማስፋፋት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ቁርጠኛ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ 98 በመቶ የሚሆነውን ኃይል የምታመነጨው ከንፁሕ ምንጮች ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የዓባይ ግድብ የአፍሪካ ትልቁ የውሃ ኃይል


"ታዳሽ የኃይል ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







## ለሀገራዊ ምክክሩ የአጀንዳ መነሻ ሀሳቦችን የማሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ ነው


ገጽ 6




መምህር ፍሬዘር ጥላሁን

# የኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት መሆን ለቀጣናው የጋራ ልማት ጠቃሚ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤትነት ቢረጋገጥ ኢትዮጵያና ቀጣናው በጋራ መልማት የሚችሉበት መልካም አጋጣሚ እንደሚፈጠር የሐሮማያ ዩኒቨርስቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ፍሬዘር ጥላሁን አስታውቀዋል፡፡


የኢትዮጵያ የባሕር በር... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


# የቃሊቲ መናኸሪያ በጥር ወር ለአገልግሎት ክፍት ይደረጋል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ እየተገነባ የሚገኘው ቃሊቲ መናኸሪያ በጥር ወር መጨረሻ ተጠናቅቆ ለአገልግሎት ክፍት የሚደረግ መሆኑን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ባለሙያ እና የቃሊቲ መናኸሪያ ግንባታ ፕሮጀክት መሪ መሐንዲስ አቶ ሚኪያስ ታደሰ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የቃሊቲ የሕዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያ ተርሚናል ግንባታ 78 በመቶ ደርሷል።

የሕዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያ ተርሚናሉ ግንባታ ተጠናቅቆ በጥር ወር መጨረሻ ለአገልግሎት ክፍት ይደረጋል ብለዋል፡፡

በአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር የሚገነባው ተርሚናሉ በአንድ ጊዜ 120 አውቶቡሶችን የማስተናገድ አቅም ያለው መሆኑን ኃላፊው ጠቅሰዋል፡፡

በሦስት ነጥብ ዘጠኝ ሄክታር ግቢ ላይ የሚገኘው ተርሚናሉ አምስት ሺህ ካሬ ላይ ያረፈ ሕንፃ ግንባታ መኖሩን ጠቅሰው፤ የተሳፋሪዎች እና የተሽከርካሪው እንቅስቃሴ በማይጋጭበት ሁኔታ የራሱ የሆነ ከፀሐይ እና ከዝናብ መከላከያ ሼድ በሕንፃው ላይ የተካተተ ነው ብለዋል።

ሕንፃው የቢሮ፣ የሱቅ፣ የካፍቴሪያ፣ የመሠብሰቢያ



አዳራሽ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ቢሮዎችን ያካተተ ሲሆን በኢትዮጵያ ሞዴል መናኸሪያ ሆኖ እየተገነባ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ቲኬት መቁረጫ ፋሲሊቲዎችን ጨምሮ የመቆያ ቦታዎች እና አውቶቡሶቹ የት እንዳሉ መረጃ የሚገኙባቸው ሲስተሞች የተሟላበት ዘመናዊ አገልግሎት የሚሰጥበት መሆኑንም አብራርተዋል።

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር መሠረተ ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሰይፉ ክንፉ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ የቃሊቲ ዘመናዊ መናኸሪያ ተርሚናል ግንባታ እስካሁን ድረስ በሀገር አቀፍ ደረጃ ካሉት መናኸሪያዎች በሞዴልነት ተወስዶ በዘመናዊ መልኩ እየተገነባ የሚገኝ ነው።


የቃሊቲ መናኸሪያ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








# የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉን የሰው ኃይል አቅርቦት ለማሳደግ እየተሠራ ነው

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉን የሠለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንደገለጹት፤ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ያለውን የሠለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት ለማሳደግ እየተሠራ ነው፡፡

በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ያለውን ብቃት ያለው የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም በዘላቂነት ለመፍታት ያለመ የሆቴል ባለቤቶች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ የዘርፉ የሙያ ማኅበራት ተወካዮችና ሌሎች የቱሪዝም ዘርፍ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት የምክክር መድረክ ሰሞኑን ተካሂዷል፡፡



የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በውይይቱ ወቅት እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፍ በሰጠው ልዩ ትኩረት አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን ለማስፋፋትና ነባሮቹንም ለማሻሻል ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው።

ጎንለጎንም ዜጎች በዘርፉ በተመረጡ የሙያ መስኮች ብቃት ያለውና የተሟላ የክህሎት ሥልጠና አግኝተው በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው በሚፈጠረው የሥራ ዕድል በመጠቀም የሥራ ገበያውን እንዲቀላቀሉ ለማስቻል ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረቱን በዘላቂነት ለመፍታት የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት በዘርፉ የልህቀት ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ በስፋት እየተሠራ ነው፡፡ የልህቀት ማዕከል ይሆናል ሲባል ከተልዕኮ በመነሳት ጥራት ያለው ሥልጠና፣ ደረጃውን የጠበቀ የምርምር ሥራ እና የላቀ ማኅበራዊ አገልግሎት ይሰጣል ማለት ነው፡፡

የልህቀት ማዕከል መሆን ከባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ትብብር ውጭ ፈጽሞ ሊሳካ እንደማይችል የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የጋራ የምክክር መድረኩ ዋና ዓላማ ኢንስቲትዩቱ ቀደም ሲል የጀመረውን ከቱሪዝም ኢንዱስትሪው ማኅበረሰብ ጋር አብሮ የመሥራት ባሕል የበለጠ በማጎልበት ጠንካራና ዘላቂ የሥራ ትብብር በመፍጠር ተልዕኮውን መወጣት የሚችልበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ላይ ያተኮረ ነው ብለዋል፡፡

በመድረኩ ተሳታፊዎች እንደተገለጸው፤ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ሙያን ማዕከል ያደረገ የክህሎት ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት ቁጥር እየጨመረ የመጣ ቢሆንም በኢትዮጵያ የሆቴል ኢንዱስትሪ እየተስፋፋ መሄዱን ተከትሎ በገበያው ላይ ሰፊ የሠለጠነ ሰው ኃይል ፍላጎት ጎልቶ ይታያል፡፡

በመድረኩ በቱሪዝም ዘርፍ በተመረቁ ሠልጣኞች፣ በሥልጠና ፕሮግራሞች ፍላጎት እና በባሕላዊ ምግቦች ዙሪያ የተሠሩ ጥናቶች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።



አቶ መስፍን ዓለሙ

# ዩኒቨርሲቲው ሁለት የልማት ፕላን ፕሮጀክቶችን አጠናቆ አስረከበ

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማማከር ቡድን ‹‹የጎጃም በረንዳ ኮሪደር›› እና ‹‹ቡልጋሪያ ቄራ›› አካባቢ የልማት ፕላን ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ለአዲስ አበባ ከተማ ፕላን እና ልማት ኮሚሽን አስረከበ፡፡

የፕሮጀክቶቹ የጥናት ቡድን አስተባባሪ የሆኑት አቶ መስፍን ዓለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ዩኒቨርሲቲው የ‹‹የጎጃም በረንዳ ኮሪደር›› እና ‹‹ቡልጋሪያ ቄራ›› አካባቢ የልማት ፕላን ፕሮጀክት የማኅበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እንዲሁም ባሕላዊ ዕሴቶችን ከግንዛቤ በማስገባት ለመኖሪያ ምቹ፤ ጤናማ እና አካታች የሆነ አካባቢን መፍጠር ዓላማ ያደረገ የልማት ፕላን ፕሮጀክት ሲሆን በአራት ወራት በማጥናት አስረክቧል፡፡

በአከባቢው ከሚኖረው ማኅበረሰብ 32 ነጥብ ሰባት በመቶ የሚሆነው ከድህነት ወለል በታች የሚኖር መሆኑን በመጥቀስ፤ በርካታ ዜጎች በአካባቢው ላይ ሥራ አጥ መሆናቸውን በጥናቱ ላይ እንደተገኘ ተናግረዋል፡፡

በመሬት አጠቃቀም ዙሪያም ክፍተት መኖሩን እንዲሁም በአካባቢው የመልማት ፍላጎት ቢኖርም የአቅም ማነስ ችግሮች መኖራቸው በጥናቱ መመላከቱን ገልጸው፤ በጥናቱ የመፍትሔ አቅጣጫ ተብሎ የተቀመጠውም የግል እና የመንግሥት ተቋማት በጋራ በመሆን በስምምነት የገንዘብ እና የመሬት ትስስር በመፍጠር አካባቢውን ማልማት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው የሚኖሩት አራት ሺ 521 ነዋሪዎች ቢሆኑም በፕሮጀክቱ አከባቢውን የሚመጥኑ እስከ 105 ሜትር ከፍታ ያላቸው ፎቆች በመገንባት 27 ሺህ የሚሆኑ ነዋሪዎችን መያዝ እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡

የጎጃም በረንዳና አውቶቡስ ተራ አካባቢዎች ግዙፍ የንግድ እንቅስቃሴዎች፣ የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች የሚከወኑበት፣ ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ መንገደኞች መዳረሻ እና የፌደራል የመንግሥት ተቋማት የሚገኙበት እንደመሆኑ እስካሁን አካባቢውን የሚመጥን የልማት ሥራዎች በበቂ ሁኔታ አለመሠራታቸውን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ይህ አካባቢ ትልቅ የመልማት አቅም ካላቸው ቦታዎች መካከል በቀዳሚነት እንደሚጠቀስ ገልፀዋል፡፡

ይህ ጥናት ሲደረግ ማኅበረሰቡን በማሳተፍ የችግሮች የመፍትሔ አካል እንዲሆኑ ተደርጎ መሠራቱን የጠቆሙት አቶ መስፍን፣ የፕሮጀክት ሥራው የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች ያሳተፈ መሆኑንና ተማሪዎቹ በተግባር የመስክ ሥራዎችን እንዲማሩ እና እውቀታቸውን እንዲያሳድጉ የረዳ እንደነበር አስረድተዋል፡፡

በልማት ፕሮጀክቱ ጥናት ላይ ከተለያዩ የሙያ መስክ ማለትም አርክቴክቸር ፤የከተማ ፕላን፤ ኢኮኖሚክስ እንዲሁም የማኅበረሰብ ጥናት ምሑራን እንደተሳተፉበትም ጠቁመዋል፡፡

ቄራ፤ ቡልጋሪያ እና ቴሌ አካባቢ የሚከናወነው ፕሮጀክት 79 ሄክታር የሚሸፍን ሲሆን የጎጃም በረንዳ-አውቶቡስ ተራ አካባቢ ፕሮጀክት ደግሞ 33 ነጥብ 9 ሄክታር መሬት የሚሸፍን እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

# ‘‘ግድቤን በደጄ’’ የተሰኘው የውሃ ሽፋንን የማሳደግ የሙከራ ፕሮጀክት ውጤታማ ሆኗል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ከጣሪያ ላይ የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ የውሃ ሽፋንን ለማሳደግ በሙከራ ደረጃ የተጀመረው "ግድቤን በደጄ" የተሰኘ ፕሮጀክት ውጤታማ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የውሃና ኢነርጂ እና የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የውሃ አማራጭን ለማስፋት የሚያስችል "ግድቤን በደጄ" የተሰኘ ፕሮጀክት በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት አድርገዋል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ በወቅቱ እንደገለጹት፣ የ"ግድቤን በደጄ" ፕሮጀክት የጣሪያ ላይ የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ ተጨማሪ የውሃ ሀብት አቅምን ለመፍጠር የሚያስችል ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የውሃ ጥምን የሚወጣው ተጨማሪ የውሃ አማራጮችንም በመጠቀም ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ውሃን በአማራጭ በማሰባሰብ ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ላይ እየተሠራ እንዳለ ጠቅሰው፤ በዚህ ላይ ትኩረት ያደረገው ፕሮጀክቱ በሙከራ ደረጃ ተጨባጭ ውጤት ማምጣቱን ገልጸዋል፡፡

በተለይም ዝናብ አጠርና ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ፕሮጀክቱን በሰፊው ለመተግበርና ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በትኩረት እየተሠራ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡

ከጣሪያ ላይ የዝናብ ውሃን የማሰባሰብ ቴክኖሎጂን በማስፋፋት የውሃ አቅርቦትን ለማሳደግ በሰፊው እንደሚሠራ ገልጸው፤ የውሃ እጥረት ባለባቸውና በተደጋጋሚ በድርቅ ተጎጂ ለሆኑ ሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የፕሮጀክቱ ትግበራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡ ለሥራው መሳካት የአጋር አካላት ሚና ከፍተኛ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡



ፎቶ በገባቦ ገብሬ

ኢትዮጵያ በውሃ ሀብት የታደለች አገር መሆኗንና ይህንን ፀጋዋን በቴክኖሎጂ አስደግፋ መጠቀም እንዳለባት ሚኒስትሩ ጠቁመው፤ ለዚህ ደግሞ ግድቤን በደጄ ፕሮጀክት አንዱ ማሳያ እንደሆነና የንጹሕ መጠጥ ውሃ ሽፋንን በማሳደግ የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ የሚችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር የተካሄደው የድርጊት ስምምነት ዘርፉን ከሥራ ዕድል ጋር ለማስተሳሰር አጋዥ መሆኑንም ሚኒስትሩ ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በሙከራ ተጨባጭ ውጤት እንዳስገኘ በመጥቀስ፣ በቀጣይ በስፋት ወደ ሥራ ሲገባ ለበርካታ ወጣቶች የሥራ እድልን እንደሚፈጥር ተናግረዋል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው፣ ፕሮጀክቱ ዜጎች የተፈጥሮ ፀጋን በአግባቡ በመጠቀም በራሳቸው የውሃ ባለቤት መሆን የሚችሉበትን እድል የሚፈጥር እንደሆነ ገልጸዋል።

ግድቤን በደጄ ፕሮጀክት ተጨማሪ የሥራ እድል ለመፍጠር ጉልህ ሚና እንዳለው ጠቅሰው፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በዘርፉ የሠለጠኑ ወጣቶችን በማሠማራት የሥራ ዕድል ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥ ሥራ እንደሚሠራም አስታውቀዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ ሲዳማ እና በቀድሞ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ባሉ 87 ትምህርት ቤቶች ላይ ሲተገበር መቆየቱ ተገልጿል፡፡

# በአማራ ክልል በ1 ነጥብ8 ሚሊዮን ሔክታር መሬት ላይ የለማው የመኸር ምርት ተሰብስቧል

## - በበጋ መስኖ ልማት ከ40 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በ2015/16 የመኸር እርሻ ከለማው መሬት ከአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ያለ ምርት መሰብሰቡን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በበጋ መስኖ ልማት ከ40 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል፡፡

የቢሮው ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ቃልኪዳን ሽፈራው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015/16 የመኸር እርሻ ሥራ ከለማው አምስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት እስካሁን በአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የሚገኝ ሰብል ተሰብስቧል።

ሰሊጥ፣ ማሾ፣ አኩሪ አተርና የቢራ ገብስ ከሌሎች ሰብሎች ቀድመው የደረሱ በመሆናቸው በዘመናዊና በባሕላዊ መንገድ በመታገዝ ሰብል የመሰብሰብ ሥራው በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

በክልሉ ሰፊ የምርት ሽፋን ያላቸውን የስንዴ፣ የጤፍና የበቆሎ ሰብሎችን የመሰብሰብ ሥራ የተጀመረ ሲሆን፤ በዘመናዊ መንገድ ለመሰብሰብ በክልሉ ከሚገኙ ባለሀብቶችና ማኅበራት ኮባይነር የማስገባት እንቅስቃሴ ተጀምሯል ብለዋል፡፡

በተጨማሪ ትምህርት ቤቶችን በማስተባበር ተማሪዎችና መምህራን ለሰብል ስብሰባው እገዛ እንዲያደርጉ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።



በክልሉ ከአንድ ሄክታር በአማካኝ 31 ነጥብ ሁለት ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በአጠቃላይ በክልሉ በዘር ከተሸፈነው መሬት 160 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

በክልሉ የሚገኙ ቀድመው የደረሱና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ እንዲሁም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ወደተለያዩ ሀገራት መላክ መጀመራቸውን አመላክተዋል፡፡

በምርት ዘመኑ የግብዓት አቅርቦት፣ የፀጥታ መደፍረስ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የዝናብ እጥረት ተግዳሮት እንደነበሩ አስታውሰው፤ አሁን ላይም ያለው የፀጥታ ሁኔታ ኮምባይነርን ከቦታ ቦታ አንቀሳቅሶ ምርት ለመሰብሰብ ፈታኝ እንዳደረገው አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪ በክልሉ በሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ መኖሩን ጠቁመው፤ የደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ሳይደርስ በወቅቱ እንዲሰበሰቡ በየደረጃው ላሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ለግብርና ባለሙያዎች ግንዛቤ የመፍጠር፣ የሚቲዎሮሎጂ ትንቢያዎችን የማስተላለፍ እና ዘመናዊ የመሰብሰቢያ መሣሪያዎችን ወደክልሉ የማስገባት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በተያዘው ወር መጨረሻ ድረስ የጥራጥሬ ሰብል ምርቶችን የመሰብሰብ ሥራው የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ ሌሎች ሰብሎችን እስከ ጥር አጋማሽ ድረስ የመሰብሰብ ሥራ እንደሚከናወን አስረድተዋል።

በተያዘው የበጋ ወቅትም ከ333 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በነባርና በአዲስ የመስኖ አማራጮች በማልማት 40 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ ወደ ሥራ መገባቱን ገልጸዋል፡፡

በመስኖ ከሚለማው ጠቅላላ መሬት ውስጥ 250 ሺህ የሚሆነው በበጋ መስኖ ስንዴ የሚሸፈን ሲሆን፤ ዘጠኝ ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታሉ ምርት እንደሚጠበቅ አመላክተዋል።

በሁሉም አካባቢዎች የበጋ መስኖ ሥራው ምን ላይ ማተኮር እንዳለበትና ከመቼ እስከመቼ ይጠናቀቃል የሚለውን የጋራ ለማድረግ በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት መደረጉን አመላክተዋል፤

እስካሁን 81 ሺህ ሄክታር መሬት የመለየት፣ 37 ሺህ ሄክታር መሬት በማሳረስ ከዘጠኝ ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በዘር እንዲሸፈን መደረጉን አስታውቀዋል፡፡



# በትግራይ ክልል

## በስድስት ቢሊዮን ብር ወጪ የብረታብረት ማምረቻ ሊገነባ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እና ቻይና ባለሃብቶች ትብብር በስድስት ቢሊዮን ብር ወጪ የብረታብረት ማምረቻ ኢንዱስትሪ በትግራይ ክልል ሊገነባ መሆኑ ተገለጸ። በአስር ወራት ውስጥ የሚገነባው ይህ ኢንዱስትሪ የሥራ ማስጀመሪያ መርሐ ግብር ትናንት ይፋ ተደርጓል።

የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት ጌታቸው ረዳ በመርሐ ግብሩ ላይ እንዳሉት የሌጀንድ ብረታብረት ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግለታል።

ሌሎች በግልና በማኅበር የተደራጁ ባለሃብቶችም የዚህን የልማት ፕሮጀክት አርዓያ ተከትለው በማልማት ራሳቸውንና ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የብረታብረት ማምረቻው 75 በመቶ በኢትዮጵያዊው ባለሃብት ኢንጅነር ያሬድ ተስፋይ የተሸፈነ ሲሆን ቀሪው 25 በመቶ ደግሞ በቻይናዊው ባለሃብት ሚስተር ሊ ዮን መሸፈኑን የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ ሳምሶም ገብረመድህን ገልጸዋል።

የሌጀንድ ብረታ ብረት ማምረቻ ኢንዱስትሪ 6ሺህ ለሚሆኑ ወገኖች የሥራ ዕድል እንደሚፈጥርም ተናግረዋል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ የመቀሌ ከተማ ከንቲባ ይትባረክ አመሐ በበኩላቸው ከተማ አስተዳደሩ ለሌጀንድ ብረታብረት ኢንዱስትሪ አሁን ከተሰጠው የግንባታ ቦታ ባለፈም ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን አረጋግጠዋል።

# በክልሉ ከ1 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የሕክምና አገልግሎት አግኝተዋል

## - ከ15 ሺ በላይ እናቶች በጤና ተቋማት መውለድ ችለዋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሦስት ወራት ከአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች የተመላላሽ ሕክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በክልሉ ከ15 ሺህ በላይ እናቶች በጤና ተቋማት መውለዳቸውም ተመላክቷል፡፡

የክልሉ ጤና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኢብራሂም ተማም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በሁሉም የጤና ተቋማት ባለፉት ሦስት ወራት አንድ ሚሊዮን 316 ሺህ 317 ዜጎች የተመላላሽ ሕክምና አግኝተዋል፡፡

በክልሉ በሁሉም የጤና ተቋማት ምቹና የተሟላ አገልግሎት ለዜጎች ለማድረስ በትኩረት እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በክልሉ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ በተከናወነው ሥራ ባለፉት ሦስት ወራት ከ15 ሺህ በላይ እናቶች በጤና ተቋማት መውለዳቸውን አስታውቀዋል።

በወሊድ ወቅት የሚያጋጥሙ የእናቶችን ሞት መጠን ለመቅነስ የሚያስችሉ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸው፤ ነፍሰ ጡር እናቶች በጤና ተቋማት እንዲወልዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በሰፊው መሠራቱን አስረድተዋል፡፡

በክልሉ የእናቶች ጤና እንክብካቤ፣ የቅድመ-ወሊድና የድህረ-ወሊድ ክትትሎች ላይ በተከናወነው ሥራ ካለፈው ዓመት የተሻለና መልካም ውጤት መገኘቱን ኃላፊው አመላክተዋል።

በክልሉ የሚገኙ 183 ሺህ ዜጎች በተለያዩ የጤና ተቋማት የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድሕን ተጠቃሚ መሆን ችለዋል ያሉት አቶ ኢብራሂም፤ በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድሕን 79 ሚሊዮን ብር መሰብሰቡን ገልጸዋል፡፡

በክልሉ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድሕን የግንዛቤና የሽፋን መጠኑ እያደገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሁሉም ሰው



**አቶ ኢብራሂም ተማም**

በቂና ፍትሐዊ አገልግሎት እንዲያገኝ እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ቀደም ሲል ዜጎች ለሚያጋጥማቸው ሕመም የሕክምና አገልግሎቶችን በበቂ ሁኔታ እንደማያገኙ ጠቅሰው፤ የጤና መድሕን አገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑ በኋላ በ500 ብር መዋጮ የተለያዩ ሕክምና አገልግሎቶችን ዓመቱን ሙሉ እያገኙ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በክልሉ ውስብስብ ሕክምናዎችን ለመስጠት የሚያስችል የሪፈራል ሆስፒታል እጥረት በመኖሩ አርሶና አርብቶ አደሮች ወደ ሩቅ ቦታዎች በመጓዝ ለተጨማሪ የሕክምና ወጪ እየተዳረጉ መሆኑንና በዚህም ዜጎች ችግር ላይ መውደቃቸውን ገልጸዋል፡፡

የሪፈራል ሆስፒታል ግንባታ ተፈቅዶ ዜጎች የተሻለ የሕክምና አገልግሎቱ በቅርበት እንዲያገኙ የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለዓባይ ግድብ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥል!

በዓባይ ወንዝ ላይ፣ ሕልም በሃሳብ ተደግፎ፤ ምኞትን በትልም ተነድፎ፤ ትልም በተግባር ተቀይሮ፤ ድሮ ሕልም የነበረው ዛሬ በብርሃኑ ወጋገን ማራመድ ሲጀምር፤ የትውልድ ባለታሪክነት፣ የመሪነትም ልዕልና ተገልጧል፡፡ ምክንያቱም ቀደምቶቻችን አስበውና አልመው በንድፍ ያኖሩት ዓባይ፤ ዛሬ በእኛ ዘመን ንድፉን ተመልክተን፣ ሕልምና ምኞታቸውን ተላብሰን ዓባይን ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት እንዲውል ገድበን የታለመው ብርሃን እውን እንዲሆን አድርገናል፡፡

ይሄን ስናደርግ ቀደምቶቻችን የተፈተኑበትን ችግር በመገንዘብ፤ በልመና ሳይሆን በራስ አቅም ለመገንባት የፋይናንስ ምንጭ ራሳችን እንድንሆን ተልመን ነው፡፡ የቀደሙትን ሕልምና ትልም ወደ ተግባር መለወጥ የቻለው የዛሬው ትልውድ ታዲያ፤ በራሱ ተልሞ ሊተገብር ያሰበውን ከመፈጸም የሚያግደው የለምና በራሱ የፋይናንስ አቅም ጀምሮ እነሆ በብርሃን ታጅቦ ወደ ፍጻሜው ጫፍ ደርሷል፡፡

በዚህ መልኩ መንግስት እና ሕዝብ ተባብረው ለመገንባት የወጠኑት የዓባይ ግድብ፤ መንግስት ለግንባታው ካዋለው ወጪ ውስጥ ከ18 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላዩ ኢትዮጵያውያን ከሕጻን እስከ አዛውንት፣ ከጉልት ቸርቻሪ እስከ ባለሃብት፣ በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጪም ያሉ ኢትዮጵያውያን ተባብረው ለዚህ ግድብ እንዲውል ያዋጡት ገንዘብ ነው፡፡

ኅብረተሰቡ በልገሳ፣ በቦንድ ግዢ፣ በቶምቦላ፣ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት (8100 A)፣ በሕዳሴው ዋንጫ እና በሌሎችም መንገዶች ግንባታው እውን ከሆነበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ድጋፋቸውን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ተማሪው ከወላጆቹ የምትሰጠውን የኪስ ሳንቲም ቆጥቦ፤ የመንግስት ሰራተኛው ከወር ደመወዙ አርሷደሩ ከምርቱ ቀንሶ፤ አርብቶ አደሩ ከእንስሳቱ ቆጥሮ፤ ነጋዴው ከትርፉ አውጥቶ፤ ዳያስፖራውም ባለበት አቅሙ የፈቀደውን ተሳትፎ አድርጎ ሁሉም አለኝታነቱን አረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ሀብት ማሰባሰብ የሕዝብ ድጋፍን አጠናክሮ የማስቀጠል እንቅስቃሴን በተመለከተ ባወጣው መግለጫ እንዳመለከተው፤ ባንኩ ለግድቡ ግንባታ እና ለኃይል ማስተላለፊያ ግንባታ ፕሮጀክት የሚውል ከ149 ነጥብ 82 ቢሊዮን ብር በላይ ብድር በማቅረብ የግድቡን ፍጻሜ እውን እያደረገ ይገኛል።

ከዚህ ባሻገርም ዜጎች ለግድቡ የሚያደርጉትን ድጋፍ የማሳለጥ ተግባርን እየከወነ ሲሆን፤ በዚህም እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30/2022 ድረስ በብር እና በውጭ ሀገር ገንዘብ ለሕዳሴው ግድብ የተደረገው ሃብት ማሰባሰብ ተግባር ጉልህ ነው፡፡ በዚህም በባንኩ በኩል ከስምንት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ የቦንድ ሽያጭ ተከናውኗል፡፡ ከ208 ሚሊዮን ብር በላይም ለግድቡ ግንባታ የሚውል ገንዘብ ከዜጎች በልገሳ ተገኝቷል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ ከውጪ ሀገር ቦንድ ሽያጭ በውጪ ምንዛሬ 37 ሚሊዮን ዶላር፣ ሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዩሮ፣ እና አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ፓውንድ ገቢ ተደርጓል፡፡

በሌላ መረጃ ደግሞ፣ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የግድቡ ግንባታ አፈፃፀምና የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 12ኛ ዓመት በዓል አከባበር በተመለከተ በ2015 ዓ.ም ማገባደጃ ላይ ምክክር ባደረገበት ወቅት እንደተገለጸው፤ የግድቡ የመሰረት ድንጋይ ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ 18 ቢሊዮን ብር በተለያዩ መንገዶች ለግድቡ ግንባታ ከኅብረተሰቡ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

ይሄ ደግሞ ሕዝቡ ለግድቡ ከፍጻሜ መድረስ እያደረገ ያለው ተግባር በእጅጉ ከፍ ያለ መሆኑን የሚጠቁም ሲሆን፤ ይሄው የሕዝብ ተሳትፎ (በገንዘብም፣ በጉልበትም) እንደ እስካሁኑ ሁሉ በዚህ በጀት ዓመትም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የዚህ ማሳያው ደግሞ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት በ2016 በጀት ዓመት ለመሰብሰብ ካቀደው ከአንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ውስጥ፤ በበጀት ዓመቱ ሁለት ወራት ብቻ በተለያየ መንገድ ከ297 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉ ነው፡፡ እስካሁንም ከ18 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ በተለያየ አግባብ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በዚህ መልኩ ሁሉም ዜጎች፣ ሁሉም የከተማ አስተዳደሮች፣ ሁሉም ክልሎች የየራሳቸውን ዐሻራ እያሳረፉ ይገኛል፡፡ ከሰሞኑም የኦሮሚያ ክልል እንዳስታወቀው ደግሞ፣ በዚህ ዓመት እንደ ክልል አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ለዓባይ ግድብ ግንባታ የሚውል ሃብት ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ለዚህም "ቃላችንን እናድሳለን" በሚል መሪ ሃሳብ በክልል ደረጃ ለግድቡ ግንባታ የሀብት ማሰባሰቢያ ንቅናቄ ተጀምሯል፡፡

በ2015 ዓ.ም በክልሉ ከአንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ በመሰብሰብ ከፍ ያለ የሕዝብ ተሳትፎ የታየ መሆኑን የገለጸው የኦሮሚያ ክልልም፤ የዚህ ዓመት እቅዱም እንደ ሀገር ካለው ተሳትፎ ጋር ሲዳመር ለግድቡ ከፍጻሜ መድረስ አበርክቶው ከፍ ያለ መሆኑም ነው የተጠቆመው፡፡ በመሆኑም እንደ ሀገርም፣ በየክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በዚህ መልኩ የሚደረገው ድጋፍና ተሳትፎ እንደ ቀደመው ሁሉ ዛሬም የቀጠለ ሲሆን፤ ይሄም ግድቡን ለማጠናቀቅ የሚጠይቀውን ሃብት ለማሳካት የሚያግዝ እንደመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በማስተዋል ያልተደገፈው የዋጋ ጭማሪ

ግርማ መንግሥቴ

ሁሉም ነገር ደርዝ አለው። ሁሉም ነገር ልክ አለው። ደርዝ የሌለው፤ ልክ የሌለው፤ በማስተዋል ያልተደገፈ ነገር ሁሉ፣ ይዋል ይደር እንጂ ለማንም አይበጅም።

አሁን አሁን እየታየ ያለው ነገር ሁሉ ይኸው ነው፤ ደርዝ የለውም፤ ልክ የለውም፤ በማስተዋል የተደገፈ፣ በግንዛቤ የተቃኘ፣ ኢትዮጵያዊ ባሕልንም ሆነ ማንነትን (የኢኮኖሚንም ይሁን ሌላ) ያገናዘበ አይደለም።

ይሉኝታ የለውም፤ ወገናዊነት አይታይበትም። "እኔ ከሞትኩ . . ." እንዳለችው እንስሳ ሊሆን የቀረው ምንም ነገር የለም። ጉዳዩን በአንድ ነገር ላይ ብቻ አተኩረን እንመልከተው።

ይህ ጸሐፊ ስራውም ውሎውም 4 ኪሎ ነው። የድሮውን እንተወውና የአሁኑን ዘመን አራት ኪሎ በሚገባ ያውቀዋል። ያሉት ነገሮች በቤት ቁጥር፣ በንግድ መደብር ደረጃ ይታወቃሉ።

በመሆኑም፣ ምን ስንት ነበር፤ አሁን ስንት ገባ? ስንት ጭማሪ አሳየ፣ ምክንያቱስ? የሚሉትን ሁሉ (ያው የኪስ ጉዳይ ነውና) ይታወቃሉ። በመሆኑም፣ ጤነኛውን ከበሽተኛው መለየት ላይ ችግር የለም ማለት ነው። የጀበና ቡናን ወስደን እንመልከት።

የጊዜ፣ የዘመን ጉዳይ ሆነና ገበያውን የተቆጣጠረው የጀበና ቡና ነው። እኛ መጀመሪያ የጀመሩት ሴትዮ ምስጋና ይግባቸውና ዛሬ የጀበና ቡና ከትላልቅ ቢዝነሶች ተርታ እየተሰለፈ ነው። በተለይ ከታክሲና መሰሎቹ ነፃ መሆኑ ባለቤቱን ፈርጠም ለማድረግ ጊዜ አይፈጅበትም።

ይህ ባልከፋ። ሰርቶ ማግኘት የሚጠበቅ ነውና ያስደስታል። ነገር ግን ይህ "ሰርቶ ማግኘት"፤ "ነግዶ ማትረፍ" የሚሉት ነገር እያወዛገበ የመሆኑ ጉዳይ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ገበያው ከስነምግባር ማፈንገጡ ብቻ ሳይሆን፣ በዘርፉ የሚታዩ ተግባራት በማስተዋል የሚከናወኑ ሲሆኑ አለመታየታቸው ነው።

እዚህ 4 ኪሎ የጀበና ቡና፣ የአንዱ ስኒ ዋጋ ግራ በሚያጋባ ደረጃ በየቀኑ ለማለት ቅር እስከማይል ድረስ ዋጋው እየተቆለለ፤ ለጠጪው ሳይሆን ለራሱ፣ ለሻጩ ሳይቀር እየገረመው ይገኛል።

ከወር በፊት 15 ብር የነበረ የአንድ ስኒ የጀበና ቡና ዋጋ፣ ምንም ሳይታሰብ 20 ላይ ጉብ ብሎ ተገኘ። ይህ አይደለም የሚገርመው፤ የሚገርመው በ20 ከሳምንት በላይ ሊዘልቅ ሳይችል ቀርቶ እነሆ 25 ብር ላይ ተገማሽሮ ተቀምጧል። "ምክንያት?" ሲባል፣ ምንም፤ ዝም፣ ጭጭ።

በመሰረቱ፣ ፎቆች ኮሪደሮቻቸው ለሕንፃው ተጠቃሚዎች መንቀሳቀሻ ይሆኑ ዘንድ ታስበው ነበር የተገነቡት፤ መሆን ያለበትም ያ ነበር። እሱ ቀረና እያንዳንዷ ካሬ ተሸንሽና (የየመፀዳጃ ክፍሎቹ ፊት ለፊት ሳይቀር) ለጀበና ቡናና ኮስሞቲክስ "መደብር" ተከራየች። ያ ሌላ ታሪክ ነውና ወደ ቡናችን እንመለስ።

አንዳንድ የጀበና ቡና ነጋዴዎች ለዋጋ መጨመር ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡ "ኪራይ ጨመሩብን" የሚል ነው። እንደዚህ ፀሀፊ ከሆነ ይህ በፍፁም አያሳምንም። ወይም፣ እንደዛ የሚያደርግ ባለ ፎቅ ካለ፤ በየ15 ቀኑ ኪራይ የሚቆልል ባለሀብት ከሆነ እሱ በቀጥታ ወደ አማኑኤል ማቅናት ይገባዋል።

**አንዳንድ የጀበና ቡና ነጋዴዎች ለዋጋ መጨመር ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡ "ኪራይ ጨመሩብን" የሚል ነው። እንደዚህ ፀሀፊ ከሆነ ይህ በፍፁም አያሳምንም። ወይም፣ እንደዛ የሚያደርግ ባለ ፎቅ ካለ፤ በየ15 ቀኑ ኪራይ የሚቆልል ባለሀብት ከሆነ እሱ በቀጥታ ወደ አማኑኤል ማቅናት ይገባዋል**

ምክንያቱም፣ መቸም አይደለም የሕንፃ ኮሪደር፣ የሕንፃው ቢሮ እንኳን ቢሆን ቢያንስ ከሁለት ዓመት በታች ውል የለምና ነው። በመሆኑም የባለ ጀበናዎቹን ዋጋ መጨመር ከኪራይ መጨመር ጋር ማያያዝ ውሀ የሚቋጥር አይሆንም።

አንድ ባለ መደብር አዛውንት በዚሁ ጉዳይ ላይ ስናወራ የተናገሩት ነገር ለቁም ነገር የሚበቃ ነው። "አዛውንቱ የዛሬ ነጋዴዎች አንድ ነገር ይይዛሉ፤ ከእሱው ላይ ስንጥቅ በማትረፍ መክበር ይፈልጋሉ። ንግድ እንደሱ አይደለም። በንግድ ዓለም ትርፍ የሚገኘው ከብዛት ነው። የሸቀጥ፣ እቃዎችን አይነት ማብዛት፤ ከእነዛ ላይ መጠነኛ ትርፍን ማግኘት። ያ ተሰባስቦ ነው ትርፉን ጥሩ የሚያደርገው" ነበር ያሉት።

እውነታቸውን ነው። ከዛ በኋላ ልብ ብለን ስንመለከት ያየነው ነገር ቢኖር እሳቸው ያሉትን ነው። አብዛኛው ነጋዴ ሸቀጦችን በብዛት የያዘ ነው። ሱቆች ተቆጥሮ የማያልቅ ሸቀጦች አሏቸው። ቡና ቤቶች፣ የልብስ መደብሮች ወዘተ በርካታ አይነቶችን ነው ይዘው የሚቀርቡት።

ወደ ጀበና ቡና ነጋዴዎች ስንመጣ ግን አብዛኞቹ ቡና ብቻ እንጂ፣ ሻይ እንኳን የላቸውም። ብስኩት፣ ሳንቡሳ፣ የፕላስቲክ ውሀ . . . አያቀርቡም። ማስቲካ፣ የሞባይል ካርድ ወዘተ የላቸውም። ሙሉ ለሙሉ ማትረፍ የሚፈልጉት ከአንድ ነገር ብቻ ነው፤ ከቡናው።

እድሜ ለባለ ጀበና ቡና ባለቤቶች፣ ዛሬ ዛሬ የቡና አገር ሰው ሆኖ ቡና የማይጠጣው ሰው ቁጥሩ እየበዛ እየሄደ፤ የሚጠጣው ሰው እየቀነሰ ነው። አንድ ስኒ ቡና 25 ብር ከሆነ፤ እንዴት ሆኖ ነው ሁሉም ሰው፣ በተለይም የቡና ሱስ ያለበት ሁሉ በ25 ብር አንድ ስኒ ቡና የሚጠጣው? በቀን አራት ጊዜ እንጠጣ ብንል እኮ 100ዋን ቁጭ አደረግን ማለት ነው። ይህ ለብዙሀኑ የሚቻል ነው?

እዚህ ላይ አንድ በጣም የሚገርም ጉዳይ አለ። አብዛኞቹ የጀበና ቡና ነጋዴዎች በአንድ ሰው የሚስተናገዱ ናቸው። "የሰራተኛ ደሞዝ" ይሉ ጣጣ የለባቸውም። አጨማመራቸው ግን 5 ብርን በአንድ ብር ቦታ በማስቀመጥ ነው ዋጋ የሚቆርጡት።

ገና ለገና አዲስ አበባ የሰው ጫካ ሆናለችና ከዚህ ሁሉ ውስጥ ለኔ የሚሆን አላጣም ከሚል የተሳሳተ መነሻ ሁሉ ይመስላል ነግቶ ሲመሽ ዋጋ መቆለል ነው፤ 4 ኪሎ እየሆነ ያለው ይሄ ነው።

ዛሬ እኮ ትንሹ የጀበና ቡና ዋጋ (በስኒ) 15 ብር ነው - የሚረባውም፣ የማይረባውም፤ በመንግስት ቤት የሚነግደውም፣ በሰው መሄጃ መንገዶች ላይ ላስቲኩን ወጥሮ ቁጭ ያለውም፤ ቀበሌውም። ሁሉም ከማን አንሼ ነው መሰለኝ ስራቸው ገበያ ማረጋጋት ሳይሆን ገበያውን ማጦዝና አብዛኛውን የማሕበረሰብ ክፍል ከገበያ ማስወጣት ነው።

የድሮዋ እናት 4 ኪሎ ዛሬ ይሄንን ነው የምትመስለው። መጨመር፣ መጨመር፣ የት ጋ ስምምነት ላይ እንደሚደርሱ ባይታወቅም በተመሳሳይ ሰዓትና ቀናት ሁሉም ተመሳሳይ የዋጋ ጭማሪ ላይ ይገኛሉ። እፍረት የለም፤ በ4 ኪሎ ሰሞኑን እየታየ ያለው ይሄ ነው።

አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አንድ ስኒ የጀበና ቡናን ከ15 ብር አንስቶ 25 ላይ ማድረስ ምን ይባላል፤ የጤና ነው? በዚህ ከቀጠለስ ምን አይነት ኢኮኖሚያዊ እድገት ይመልሰዋል?

እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ማለት ያስፈልጋል፤ ሻጭም በተመሳሳይ ሁኔታ ሸማች መሆኑን። ግሸበት አገርን ነውና የሚጎዳው እሱ በጆንያ ሰበሰብኩ ሲል መልሶ በጆንያ ወስዶ ያስረክበዋል። በቃ፣ ይኸው ነው።

ከሁሉም በፊት፣ ሁላችንም ከመጎዳታችን በፊት፤ አብዛኛውን የሕብረተሰብ ክፍል ከገበያው ከማስወጣታችን በፊት . . . በፊት . . .በፊት፤ ቆም ብለን ልናስብ፣ ውሳኔዎቻችንንም በማስተዋል ልናደርግ ይገባል። ባጭሩ፣ የአቦይን ትዝብታዊ አነጋገር እንዋስና በ"እየተስተዋለ" ትዝብታችንን እናጠቃልል።

# ለሀገራዊ ምክክሩ የአጀንዳ መነሻ ሀሳቦችን የማሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ ነው

**ማርቆስ በላይ**


አዲስ አበባ፡- በአስራ አንድ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሀገራዊ ምክክሩ የተሳታፊ ልየታና የአጀንዳ መነሻ ሀሳቦች የማሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር) አስታወቁ። ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምክክሩ ዋና መድረኮች አስቀድሞ በሁሉም አካባቢዎች ክልላዊ ሀገራዊ ምክክር ይካሄዳል።

ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ከሚገኙ 13 ክልሎች በ11ዱ ላይ የተሳታፊ ልየታና የአጀንዳ መነሻ ሀሳቦች የማሰባሰብ ሂደት ማከናወን ተችሏል።

የአጀንዳ መነሻ ሀሳቦች የማሰባሰብ ሥራዎችን በጥንቃቄ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት ተደርጎ ወደተግባር መግባቱን ያመለከቱት ዶክተር ዮናስ፣ በ2016 ዓ.ም አጋማሽ ይካሄዳል ተብሎ ለሚጠበቀው ሀገራዊ ምክክር አስፈላጊ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የተባባሪዎች ሥልጠና በኦሮሚያ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ በሱማሌ ክልል ላይ መሰጠቱን ጠቅሰው፤ በትግራይና አማራ ክልሎች ቀሪ ሥራዎች እንደሚከናወኑ አመላክተዋል።

በኦሮሚያ ክልል ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችና ከዩኒቨርሲቲ ምሑራን ለተውጣጡ የተባባሪ አካላት ጋር የልምድ ልውውጥና ሥልጠና ተሰጥቷል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በተለይም ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከመምህራን፣ ከአባገዳዎች፣ ከአደ ሲንቄዎችና ከእድሮች ለተውጣጡ ዜጎች ሥልጠና



**ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር)**

መሰጠቱን ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የሀገራዊ ምክክሩ የአስተባባሪዎች ሥልጠና ከመስጠት ባለፈ የተሳታፊዎች ልየታና የአጀንዳ መነሻ ሀሳቦች በመቅረብ ላይ መሆናቸውን ገልጸው፤ በአማራ ክልል ወደ ዋና ተግባር ለመግባት ከክልሉ ምሑራን፣ ከሲቪክ ማኅበራትና አመራሮች ጋር ውይይት እየተካሄደ ይገኛል ብለዋል፡፡

በትግራይ ክልል ከጊዜያዊ አስተዳደሩና አማካሪዎች ጋር ተስፋ ሰጪና የሚያበረታታ ውይይት መደረጉን ጠቁመው፤ በተለይም ከዩኒቨርሲቲዎችና ከሲቪል ማኅበራት ጋር ንግግር በመጀመሩ በቀጣይ ሥልጠናዎች እንደሚሰጡ አመላክተዋል።

ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምክክሩ በፊት በሁሉም አካባቢዎች ክልላዊ ሀገራዊ ምክክር እንደሚካሄድ የገለጹት ዶክተር ዮናስ፤ ከቀበሌ፣ ወረዳና ዞኖች የተመረጡ ተሳታፊዎች በክልል ደረጃ ምክክር እንደሚያካሂዱ አስታውቀዋል።

በቀጣይ የምክክሩ መርሕ አካታችነት በመሆኑ ሁሉንም ባሳተፈ መልኩ በሀገር ውስጥና በውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበት መሆኑን ተናግረው፤ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀሪ ሥራዎች በትኩረት እንደሚከናወኑ አስረድተዋል።

በውጪ ሀገራት የሚገኙ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በምክክሩ ለማሳተፍ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ጋር የመጀመሪያ ዙር ንግግር መደረጉን አመላክተው፤ በውጭ ከሚገኙ ዜጎች ጋር በበይነ-መረብ አማካኝነትና በአካል ውይይት ይደረጋል ብለዋል፡፡

እስካሁን ባለው ሂደት እንቅፋቶች ቢፈጠሩም ከሕዝቡ ዘንድ ተስፋ የሚያጭሩ፣ ሞራልና ስንቅ የሚሆኑ ግብዓቶች አሉ ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በተለይም ተፎካካሪ ፓርቲዎችና ሲቪክ ማኅበራትን ጨምሮ፣ ከመንግሥትና ከሃይማኖት ተቋማት ጋር ተስፋ ሰጪ ግንኙነቶች መመሥረቱን አብራርተዋል፡፡

በሕዝቡ ዘንድ ጦርነት መፍትሔ አይደለም፤ ተመካክረን ችግሮቻችንን በውይይት እንፍታ የሚሉ ፍላጎቶች መኖራቸው ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን አመላክተዋል።

# ፌስቲቫሉ ሥራ ፈጣሪ ወጣቶችን ያበረታታል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የጀማሪ ቢዝነስ ሥነ ምሕዳር ፌስቲቫል ሥራ ፈጣሪ ወጣቶችን እንደሚያበረታታ ተገለጸ፡፡ በጂ.አይ.ዜድ የግሉ ዘርፍ ልማት በኢትዮጵያ (PSD-E) ፕሮጀክት እና በአውሮፓ ኅብረት በቢግ(DIG) ኢትዮጵያ በጋራ የጀማሪ ቢዝነስ ሥነ ምሕዳር ፌስቲቫል አካሂደዋል፡፡

በፌስቲቫል ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ባይሳ በዳዳ (ዶ/ር)፤ የኢትዮጵያ የጀማሪ ቢዝነስ ሥነ ምሕዳር ፌስቲቫል ሥራ ፈጣሪ ወጣቶችን የሚያበረታታ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ ባይሳ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ፌስቲቫሉ በሀገሪቱና በክልሎች ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማስመዝገብ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው፡፡ በፌስቲቫሉ የሀገርን ኢኮኖሚያዊ እድገት ከማስቀጠል ባለፈ ፈጣሪ ወጣቶች የፈጠራ እውቀታቸውን በመጠቀም ለራሳቸውና ለሌሎች የሥራ እድል እንዲፈጥሩ ያስችላል።

የኢትዮጵያ የጀማሪ ቢዝነስ ሥነ-ምሕዳር ፌስቲቫል ወጣቶች ያላቸውን የፈጠራና የቢዝነስ ሀሳብ በጨረፍታ ከማሳየት ባለፈ ምቹ የቢዝነስ ሥነ-ምሕዳር እንዲፈጠርላቸው ያግዛል ያሉት ኃላፊው፤ መንግሥት ለዜጎች በፈጠራና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሥራ እድል በመፍጠር የሀገርን ኢኮኖሚያዊ እድገት እያስቀጠለ



**አቶ ንጉሡ ጥላሁን**

እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ለአዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች ምቹ ሥነ-ምሕዳርና አካባቢን በመፍጠር ሚናውን እየተጫወተ ነውም ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ፌስቲቫሉ ወጣቶች ያላቸውን እምቅ የፈጠራ አቅም ተጠቅመው ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እድል የሚፈጥር መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

የሠራተኛና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን በበኩላቸው፤ ፌስቲቫሉ ጀማሪ የቢዝነስ ወጣቶችን አቅም በማጎልበት ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ የሆነ ሚና ይጫወታል ብለዋል፡፡



**ባይሳ በዳዳ (ዶ/ር)**

ፌስቲቫሉ የወጣቶች የፈጠራ ቢዝነስ ሀሳብ የሚዳብርበት ከመሆን ባለፈ ሀገሪቱ ያላትን እምቅ የሰው ኃይል እንድትጠቀም ያግዛል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ፌስቲቫሉ የሥራ ገበያ ፍላጎትና አቅርቦት የሚያሟላ፤ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ዜጎች ያላቸውን የቢዝነስ እውቀት በማዳበር ዘላቂ የሥራ እድል እንዲፈጥሩ አመቺ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነውም ሲሉ ገልጸዋል።

ለጀማሪ ወጣቶች የቢዝነስ ሥነ-ምሕዳርን በማስፋት በኩል እየተሠራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል፡፡

# የኢትዮጵያ የባሕር በር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሐሮማያ ዩኒቨርስቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ፍሬዘር ጥላሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ወደብ ለአንድ ሀገር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የኢኮኖሚ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

የባሕር በር ባለቤት መሆን የጥቅል ኢኮኖሚ እድገትን ያፋጥናል ያሉት መምህሩ፤ የማዳበሪያና የኮንስትራክሽን እቃዎችን በቀላሉና በብዛት ለማስገባት ከመርዳቱም ባሻገር፤ የውጭ ኢንቨስተሮችን በከፍተኛ ሁኔታ ለመሳብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለዋል፡፡

አቶ ፍሬዘር እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት ብትሆን ኢትዮጵያና ቀጣናው በጋራ ሊለሙ የሚችሉበት ጥሩ አጋጣሚ ይፈጥራል፤ የኢትዮጵያ ማደግና መልማት የእኔ እድገትና ልማት ነው የሚል አስተሳሰብ በቀጣናው ሊፈጠር ይገባል፡፡

ይህ ካልሆነ ግን በቀጣናው እያየን ያለነው ስደት፣ ግጭት፣ ውድመት፣ ጥፋትና የአሸባሪነት እንቅስቃሴ እየባሰ ይሄዳል የሚሉት አቶ ፍሬዘር፤ የጋራ ስምምነት አብሮ የማደግና ሰጥቶ የመቀበል መርሕን በመረዳት በጋራ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አቶ ፍሬዘር እንደተናገሩት፤ የባሕር በር ባለቤት መሆን የወጭና ገቢ ንግዶችን፣ ተቆጣጣሪ ኃይሎችንና የወደብ ቆይታ ወጭን በመቀነስ በከፍተኛ ሁኔታ የኢኮኖሚ እድገትን ያሻሽላል፡፡ ቀጣናዊ ትስስር አስፈላጊ ሆኖ የታየበት ወቅት በመሆኑ ኢትዮጵያ የባሕር በር ብታገኝ ከቀጣናው ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚ ግንኙነት እንዲኖራት ያስችላል፡፡

የባሕር በር በኢኮኖሚ ሊነሱ የሚችሉ ግጭቶችንና ኢኮኖሚ ነክ የሆኑ ፍላጎቶች የሚያስከትሉ ግጭቶችን የማስወገድ አቅም አለው፡፡ ኢኮኖሚ ሲያድግ ሰፊ የሥራ እድል ይፈጠራል፤ የዜጎች ገቢን በመጨመር በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የሚሰደዱ ዜጎችን ቁጥር ይቀንሳል፡፡ የተፈጥሮ ሀብትን መሠረት ያደረጉ የአካባቢ ግጭቶች እንዲቀንሱ ያደርጋል ብለዋል፡፡

ድህነት ለብዙ ግጭቶች መነሻ ነው ያሉት አቶ ፍሬዘር፤ በሀብት ክፍፍል በተያያዘ ለሚነሱ ግጭቶች የባሕር በሩ የአጭር ጊዜ ባይሆንም ዘላቂ መፍትሔ ለማመቻቸት የሚችል አቅም አለው ብለዋል፡፡ የቱሪዝምና የዓሣ ምርት እንደ አዲስ የሥራ እድሎችን በመፍጠር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ አወንታዊ ሚናን ይጫወታልም ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የወደብ ኪራይ ክፍያ እንዳለባት ይታወቃል ያሉት መምህሩ፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሸቀጦች ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸው ዋጋቸው ላይ ወደብ ኪራይ ይጨመርባቸዋል፡፡ የወደብ አከራይ ሀገር የሚፈጥሯቸው አሠራሮች የሸቀጦች መዘግየት፣ ጥራት መውረድ፣ የዋጋ መጨመር፣ ወደገበያ ከመግባት መዘግየትን በመፍጠር የእቃዎችን ዋጋ እንዲጨምር ያደርገዋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ይህም እቃዎች በውድ እንዲሸጡ አስገዳጅ ሁኔታን በመፍጠር ተጠቃሚዎች ላይ የዋጋ ንረትን እንደሚያመጣ የሚናገሩት አቶ ፍሬዘር፤ የወደብ ባለቤት መሆን ከተቻለ አሰልቺ አሠራሮችን በማስወገድ ሸቀጦች በተያዘላቸው ጊዜ ለተጠቃሚ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርሱ ያስችላል ብለዋል፡፡

# “ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ማመንጫ እንዲሁም ኮይሻ በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ የንፋስ፣ የፀሐይና የጂኦተርማል ምንጮችን በማስፋፋት የኢንዱስትሪ እድገት እንዲፋጠን ይሠራልም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አክለውም፤ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ከ60 ሺህ ሜጋ ዋት በላይ የታዳሽ ሃይል ሀብት አላት፤ ነገር ግን ይህንን አቅም ለመድረስ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ይጠይቃል ብለዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በአረንጓዴ ልማት የአየር ንብረት ለውጥን በመቀነስና በመላመድ ረገድ ኢትዮጵያ በአህጉሪቱ መሪ ሆና ቆይታለች፤ ከ2019 ጀምሮ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በመላ ሀገሪቱ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ 32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ከ2018 ጀምሮ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማስፋትና የድህነትን ቅነሳን ለማፋጠን ተግዳሮቶችና ያሉ እድሎችን በመለየት ማሻሻያዎች ተደርገው ሲሠራ መቆየቱን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ ሀገሪቱ ያላትን እምቅ አቅም በመጠቀም ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት እንደምትሠራም ተናግረዋል፡፡

የእኛ ራዕይ የኢትዮጵያን በተለያዩ ዘርፎች ያላትን እምቅ አቅም ሙሉ በሙሉ ለመክፈት እና ይህንን እድገት አቅም ባላቸው ተቋማት እና በሠለጠነ የሰው ኃይል ማስፋፋት ነው ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ የብልጽግና መንገድን ተከትላ ፍትሐዊ ልማትን ለማስፈን ዘርፈ ብዙ የዕድገት አማራጮችን እየተከተለች ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ የግሉ ሴክተርን የዕድገት ሞተር በማድረግ የሥነ ሕዝብ አከፋፈሏን ለምርታማነት መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በሁሉም ዘርፍ ምርታማነትን ለማሳደግና ምቹ የኢንቨስትመንት እንዲሁም የንግድ አካባቢዎችን ለመፍጠር የፖሊሲ ማሻሻያ እያደረገች መሆኗንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል።

# የቃሊቲ መናኸሪያ በጥር ወር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከዲዛይን ጀምሮ መሟላት ያለበት አስፈላጊ ፋሲሊቲ ተለይቶ እየተጨመሩለት ለአገልግሎት እየተዘጋጀ የሚገኝ ነው ብለዋል።

መናኸሪያው በዋናነት ታሳቢ ተደርጎ እየተገነባ የሚገኘው ሀገር አቋራጭ አገልግሎትን ነው ያሉት አቶ ሰይፉ፤ ተጨማሪ መሠረተ ልማት ተሠርቶም እስከ 30 እና አርባ ዓመታት ሊያገለግል የሚችል ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ በላምበረት፣ በአየር ጤና እና አስኮ የመናኸሪያዎች ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልፀው፤ እነዚህን መናኸሪያዎች ወደ ቃሊቲ መናኸሪያ ደረጃ የማምጣት ሥራ የሚሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በመናኸሪያዎች አካባቢ የሚሰጠው አገልግሎት ኢትዮጵያዊ ለሆነው ብቻ ሳይሆን አገራችን በትኩረት እየሠራችበት በምትገኘው ቱሪዝሙ ላይ ከውጭ የሚገቡ ዜጎችንም ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ይህም ቱሪስቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በትራንስፖርት ለመንቀሳቀስ ሲፈልጉ ልዩ አገልግሎት ለመስጠት በሚቻልበት ደረጃ እና በሚፈልጉት ልክ እየዘመነ የሚገኝ ነው ብለዋል።

ለግንባታው መጓተት ቀደም ሲል በስፍራው የነበረውን የፖሊስ ካምፕ ለማንሳት ጊዜ የፈጀ መሆኑ፤ የዋጋ ማሻሻያ ሂደቶች እና በመሐል የነበሩ የዲዛይን ጉዳዮች እንደምክንያት ተነስተዋል። በተጨማሪም ለግንባታው ተቋራጭ ክፍያ በወቅቱ አለመፈፀሙ ለግንባታው መዘግየት ምክንያት ነው ተብሏል፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽንና የፋይናንስ አገልግሎቶች ተደራሽነት መስፋፋት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በቴሌኮም አገልግሎቶች ተደራሽነት ላይ በስፋት እየሰራች ትገኛለች፡፡ ኢትዮቴሌኮም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይህን ስራ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በዚህም የቴሌኮም መሰረተ ልማቶችን በመላ ሀገሪቱ በመገንባት ሀገሪቱና ዜጎች ከዘርፉ ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ የዘርፉ አገልግሎት ዘመኑን የዋጀ እንዲሆን ለማድረግም የመሰረተ ልማት ማስፋፋት ስራውን አጠናክሮ በመቀጠል በሀገሪቱ የቴሌኮም አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲሰፋ የበኩሉን ሰርቷል፡፡

በዲጅታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነት በኩልም በስፋት እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ የሚያስችላትን ‹‹ዲጅታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ›› እየተገበረች ለምትገኘው ኢትዮጵያ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡ መንግስት ይህን እውን ለማድረግ ለዲጂታል ቴክኖሎጂው መስፋፋት በትኩረት እየሰራ ነው፡፡ ይህን ተከትሎም ገንዘብ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ማስተላለፍ እየተለመደ መጥቷል፡፡

የዲጂታል ግብይትና የመሳሰሉት ተግባሮች በቴሌኮም ዘርፉ ላይ ሰፊ ኢንቨስትመንት እንዲመጣ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ መንግስት የቴሌኮም ዘርፉ ለሀገሪቱና ለሕዝቧ ያለውን ፋይዳ በሚገባ በመገንዘብ ለዘመናት በመንግስት ብቻ ተይዞ የቆየውን የቴሌኮም አገልግሎት በግሉም ዘርፍ የሚከናወንበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ይህን ተከትሎም ነው ሁለተኛ የቴሌኮም ኩባንያ ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ኢንቨስት በማድረግ መስራት የጀመረው፡፡

ይህ በአፍሪካ ታዋቂ ኩባንያ በኢትዮጵያ በቴሌኮም ዘርፍ የመጀመሪያ የግል ቴሌኮም ድርጅት በመሆን ተደራሽነቱን ለማስፋት በርካታ ተግባራት ሲያከናውን ቆይቶ አገልግሎት ወደ መስጠት ከተሸጋገረ ጥቂት ዓመታት ሆነውታል፡፡

ኢትዮጵያ ደጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት ስትራቴጂ ነድፋ እየሰራች ባለችበት ወሳኝ ወቅት የሀገሪቱን የቴሌኮም ዘርፍ የተቀላቀለው ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ፣ አበረታች ለውጦች እያስመዘገበ መሆኑን በቅርቡ አስታውቋል፡፡ ኩባንያው በአገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ ለመሆን እየሰራ መሆኑን ነው የገለጸው፡፡

ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ በቅርቡ በሰጠው መግለጫ ባለፉት ስድስት ወራት የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን በመገንባት የቴሌኮም አገልግሎትን በማስፋፋት ተደራሽነቱን እያሳደገ መሆኑን አስታውቋል። በሀገሪቱ ዲጂታል ኢትዮጵያን ለማድረግ እየተከናወነ ላለው ተግባር ከፍተኛ ሚና በሚጫወተው የዲጂታል ፋይናንስ ተደራሽነት ላይ በቅርቡ በመሰማራት እየሰራ እንደሚገኝ ጠቅሷል፡፡

በመግለጫው ላይ የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ዋና ስራ አስፈፃሚ ዊም ቫንሄሌፑት፤ ድርጅቱን የተቀላቀሉት በቅርቡ መሆኑን ጠቅሰው፣ በቆይታቸውም የተለያዩ ቦታዎች መመልከታቸውን ተናግረዋል፡፡ በጉብኝታቸውም የኢትዮጵያን መልካምድር ውበትና ብዝኃነትን መመልከታቸውን ጠቅሰው፣ ይህም ሀገሪቱን ለየት እንደሚያደርጋት አመልክተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ስለኢትዮጵያ ብዙ ነገሮች እንዲያውቁ እንደረዳቸውም ይገልጻሉ፡፡

‹‹ከድርጅቱ ሠራተኞች፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከአጋሮችና ከተለያዩ አካላት ጋር ስብሰባዎችን አካሂጃለሁ፤ አሁን ከአየር ንብረቱም ሆነ ከሰው ጋር ቤተሰብ የሆንኩ ያህል ይሰማኛል›› ያሉት ዋና ስራ አስፈጻሚው፣ ‹‹እነዚህ ሁሉ ለድርጅቱ ሥራዎች ምቹ የሥራ ሁኔታና መልካም አጋጣሚዎች እንዳሉ እንድመለከት አስችለውኛል›› ብለዋል፡፡

ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ 850 ሚሊዮን ዶላር የራሱን የኔትወርክ መሠረተ ልማት ለመገንባት በኢትዮጵያ ኢንቨስት ማድረግ መጀመሩን አስታውሰው፤ ይህ ለአገሪቱም ከፍተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ነው ብለዋል። የኩባንያው ኢንቨስትመንት በመላ ኢትዮጵያ የቴሌኮም አገልግሎትን ለማስፋፋትና ሀገሪቱ ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት እየተከናወነች ለምትገኘው ተግባር ፋይዳው



የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዊም ቫንሄሌፑት

**የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ኢንቪስትመንት በኢትዮጵያ አስገራሚ ጉዞ እያደረገ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለሳፋሪኮም እድገትም ሆነ በኢንዱስትሪው ውስጥ ለማደግ ሰፊ እድል አለ። አስተማማኝ የቴሌኮም መሰረተ ልማት በመገንባት አገልግሎት ለመስጠት ትክክለኛ ቦታ ላይ መሆኑን ኩባንያው ያምናል**

ከፍተኛ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ዘርፉ ከፍተኛ ቁጥር ላለው የሰው ኃይል የስራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በቴሌኮም ዘርፉ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ ከፍተኛ ዕድል እንደፈጠረለትም ተናግረዋል፡፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፉን ከተቀላቀለ በኋላ ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን በማድረግ ረገድ በርካታ ሥራዎች እየሰራ መሆኑንም ዋና ስራ አስፈጻሚው ጠቅሰዋል፡፡

ይህ የድርጅቱ ጅምር ስራ ሁሉም ዜጋ በትንሽ ገንዘብ ጥራት ያለው የቴሌኮም አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል ነው ያሉት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ ‹‹እኛ እንደ ድርጅት የምንፈልገው በአገሪቱ ሁሉም ሰው ፈጣን እና ጥራት ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኝ ነው፤ ለዚህ ደግሞ ኃላፊነት ወስደን እየሰራን ነው ብለዋል፡፡

ዋና ስራ አስፈጻሚው እንዳሉት፤ ኩባንያው እየተከተለ ያለው የንግድ አሰራር የደንበኞቹን ፍላጎት በማወቅ መፈጸም ነው፤ በድምጽ በኩል አገልግሎቶችን በቅናሽ ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል፡፡ አሁን የፋይናንስ አገልግሎትን ለማሳለጥ የሚችሉ አዳዲስ ሥራዎች አስተዋውቋል፡፡ በዚህም በዲጅታል ፋይናንስ ዘርፉ ብዙ ሥራዎች እየሰራ ነው፡፡

ኩባንያው ወደ ኢንቪስትመንት ከገባ ከስምንት ወራት በኋላ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ የኔትወርክ መሠረተ ልማቶች ሲሰራ የቆየ ሲሆን፣ የመሠረተ ልማት ግንባታውን በአዲስ አበባና በተወሰኑ የክልል ከተሞች አካሂዷል። ወደ ስራ የገባው 500 የቴሌኮም መሠረተ ልማቶች በመገንባት ነው፡፡ እነዚህ መሰረተ ልማቶች በአሁኑ ወቅት ሁለት ሺ ደርሰዋል፡፡ በእነዚህ መሰረተ ልማቶች የተለያዩ አገልግሎቱን ተደራሽ እያደረገ ይገኛል፡፡

በአንድ ዓመት ውስጥ በ26 ከተሞችና በ254 ትናንሽ ከተሞች አገልግሎቱን እየሰጠ ነው። ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ የቴሌኮም የአገልግሎት መስጫ ቅርንጫፎቹን ሁለት ሺህ 57 ያደረሰ ሲሆን፤ ድርጅቱ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ቅርንጫፎቹን ወደ ሰባት ሺህ ለማሳደግ እየሰራ ይገኛል፡፡ ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ በቴሌኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ዘርፉ ጥራት፣ ተደራሽነትና ፈጠራ ላይ የተሻሻሉ ውጤቶችን ለማምጣት በትኩረት እየሰራ መሆኑን ነው፡፡

ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ ኩባንያው በኢትዮጵያ ባደረገው ኢንቨስትመንት አንድ ሺህ ቀጥተኛና 10ሺህ ቀጥተኛ ያልሆኑ የሥራ ዕድሎችን መፍጠሩንም አስታውቀዋል። በቀጣይ ሁለት ዓመታት ውስጥ ይህንን ቁጥር በእጥፍ ለማሳደግ እንደሚሰራ ተናግረዋል።

እንደ ስራ አስፈፃሚው ዊም ቫንሄሌፑት ገለፃ፤ አሁን ላይ አራት ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ ቋሚ ደንበኞችን ማፍራቱን ገልጸው፤ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የደንበኞቹን ቁጥር አሁን ካለበት 35 በመቶ ወደ 85 በመቶ ለማድረስም አቅዷል።

ይሄ በአንድ ዓመት ውስጥ የተሰራ የመጀመሪያ ሥራ ነው ያሉት ስራ አስፈጻሚው፤ በሚቀጥሉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ከዚህም በላይ በጣም ማሳደግ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ የቴሌኮም መሰረተ ልማቶቹን ወደ ሰባት ሺ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡ የኔትወርኩንም ተደራሽነት ለማሳደግ ተጨማሪ 600ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስት እንደሚደረግ አመልክተዋል፡፡

በቀጣይ በሚገነቡት ሰባት ሺ የቴሌኮሙዩኒኬሽን መሠረተ ልማቶች ከ80 እስከ 85 በመቶ ያህሉን ሕዝብ ተደራሽ ማድረግ እንደሚቻል ጠቅሰው፣ መሠረተ ልማቱን ለማሳደጉ ስራም እስከ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ተጨማሪ ኢንቨስትመንት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

ዋና ስራ አስፈጻሚው ኩባንያው በኢትዮጵያ ሁለት ዓላማዎችን ይዞ ነው የተቋቋመው ሲሉ ይገልጻሉ። እነዚህም የቴሌኮም አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግና የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡ ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዘርፍ ከተሰማራበት ጊዜ አንስቶ ፈጣን፣ ጥራት ያለው እና አስተማማኝ የኢንተርኔት እና የስልክ አገልግሎትን ለማስፋፋት እየሰራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ከቴሌኮም አገልግሎት ባለፈ በፋይናንስ አገልግሎትም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባለፈው ግንቦት ፍቃድ የወሰደው የሞባይል ፋይናንስ አገልግሎት ‹‹ኤምፔሳ (M-PESA)›› የተሰኘ የሞባይል መተግበሪያ ስራ ወደ ስራ መግባቱን አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የፋይናንስ አገልግሎቱ ከተጀመረ እስካሁን ድረስም አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ደንበኞች ማፍራት ችሏል፡፡ የፋይናንስ አገልግሎቱም የኩባንያውን ደንበኞችና አጋሮቹን የተሻለ ጥራት ያለውና ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡

በግማሽ ዓመት አፈጻጸሙ የዲጅታል የክፍያ ሥርዓቱ እንዲከናወንባቸው በትግበራ ላይ ከዋሉት በጂ.ኤስ. ኤም እና ኢምፔሳ የክፍያ መተግበሪያዎች አገልግሎቶች ጠንካራ የንግድ እንቅስቃሴን በማከናወን ትልቅ ምዕራፍ እያስመዘገበ መሆኑንም ዋና ስራ አስፈጻሚው ዊም ቫንሄሌፑት ጠቅሰዋል፡፡

ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ በሀገሪቱ በቴሌኮሙኒኬሽንም ሆነ በፋይናንስ አገልግሎት ዘርፉ የተለያዩ አዳዲስ አገልግሎቶች እያመጣ ተደራሽነቱን እያሰፋ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል፡፡ ለሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተደራሽነቱን ለማስፋት እንደሚሰራም አስታውቀዋል፡፡

በንግድ ስትራቴጂውም ተመራጭ የአገልግሎት አሰጣጥ አማራጮችን በመጠቀም ፈጣን፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው እና አስተማማኝ የኔትወርክ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ ሥራዎች እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህንንም የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በደንብ እንደሚያውቁት ተናግረዋል፡፡

አሁንም ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ እየሰጠ ያለው የቴሌኮም አገልግሎት በጣም ርካሽ ነው የሚሉት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ ለዚህም ከሳፋሪኮም ወደ ሳፋሪኮም የሚደረገው የድምጽ ጥሪ ሳይቀር በነጻ የሚደረግ መሆኑን በአብነት ይጠቅሳሉ፡፡ ይህም ደንበኞች ከቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ከጓደኞቻቸው ጋር እንደልባቸው እንዲነጋገሩ ወይም መረጃ እንዲለዋወጡ የሚያስችል መሆኑን አመልክተዋል፡፡

‹‹ኤምፔሳ (M-PESA)›› የተሰኘው የሞባይል መተግበሪያ ከኤኖቬሽንና ከዲጅታል ፋይናንስ አገልግሎት አንጻር ሲታይ ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ትልቅ እድል ይዞ መምጣቱን ይናገራሉ፡፡ ‹‹ኤምፔሳ›› የተሰኘውን የሞባይል መተግበሪያ ተጠቅመው መግዛትና መሸጥ የሚፈልጉ ገንዘብ ልውውጥ ለማድረግ በእጅጉ ጠቃሚ መሆኑን ገልጸው፤ ከገንዘብ ንክኪ ነጻ የሆነ ማሕበረሰብ ለመፍጠር ትልቅ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኩባንያው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ባለባት ኢትዮጵያ ሁለተኛው የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ሆኖ መግባቱን አስታውሰው፣ የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ አስገራሚ ጉዞ እያደረገ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ዊም ቫንሄሌፑት አስታውቀዋል፡፡ ‹‹ በኢትዮጵያ ለሳፋሪኮም እድገትም ሆነ በኢንዱስትሪው ውስጥ ለማደግ ሰፊ እድል አለ። አስተማማኝ የቴሌኮም መሰረተ ልማት በመገንባት አገልግሎት ለመስጠት ትክክለኛ ቦታ ላይ እንደሆንን እናምናለን ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ይሄ እንደ ባለሀብት የተለየ ከፍተኛ እድል መሆኑን አስታውቀው፣ በአገሪቱ በጣም ትልቅ ኢንቨስትመንት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ‹‹በቀጣይ ከዚህ የበለጠ ጥሩ እድል እንደሚገጥመን እናምናለን›› ሲሉ ዋና ስራ አስፈጻሚው ዊም ቫንሄሌፑት አስታውቀዋል፡፡

በቀጣይ ጊዜያት ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እየተከናወነ ባለው ተግባር ውስጥም ሆነ በቴሌኮም ዘርፍ አገልግሎቶች በመስጠት የራሱን ድርሻ እንደሚወጣም ዋና ስራ አስፈጻሚው አረጋግጠዋል፤ ድርጅቱ አሁን ባሉት ጠንካራ ሠራተኞች ጥረት አገልግሎቶችንና ተደራሽነቱን እያሰፋ ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ከሁለት ዓመት በፊት በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዘርፍ ለመሰማራት ከ850 ሚሊዮን ዶላር ምዋለንዋይ ስራ ላይ ለማዋል ፍቃድ ወስዶ ኢትዮጵያ የገባ ሁለተኛው የቴሌኮም ኦፕሬተር እንደሆነ ይታወቃል፡፡

## ወቅታዊ ትንታኔ

# ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችና የአፍሪካ ተጠቃሚነት ኢትዮጵያን እንደማሳያ

**ምሕረት ሞገስ**

እ.አ.አ በያዝነው 2023 የአፍሪካ ህዝብ ብዛት ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን በላይ መድረሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የዓለምን ሁለት በመቶ አካባቢ ሕዝብ የያዘችው አፍሪካ፤ በዓለም ላይ የሕዝብ ብዛቷን ጨምሮ ያላት የተፈጥሮ ሃብት እና ሌሎችም የተለያዩ ፖለቲካዊ ምክንያቶች ከምንጊዜውም በላይ አህጉሪቷን ተፈላጊ አድርገዋታል፡፡ ይህን ተከትሎ የተለያዩ ሀገሮች መንገዶችን እየፈለጉ ሀገሪቱን ወደራሳቸው ለመሳብ እየሞከሩ ይገኛሉ።

አፍሪካን የፈለጉ ሀገሮች አህጉሪቷን ከሚስቡባቸው መንገዶች መካከል የጋራ ጉባኤ በማዘጋጀት ትስስር መፍጠር አንደኛው ነው፡፡ ይህንን አሜሪካ፣ ቻይና፣ ፈረንሳይ፣ ሩሲያ፣ ቱርክ፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ጀርመን ከአፍሪካ ጋር የሚያስተሳስሩ ጉባኤዎችን አካሂደዋል። ቀጥታ ከአፍሪካ ጋር ብቻ ሳይሆን ከራሳቸው የቅርብ ቡድኖች ጋር በሚያካሒዱት ጉባኤ ላይም የአፍሪካን መሪዎች በመጋበዝ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ጥረት ያደርጋሉ። አሁን አስትሪያ 20ኛውን የተባበሩት መንግሥታት ኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት ጉባኤ በማካሔድ ላይ ሲሆን፤ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተጋብዘዋል፡፡ የጉባዔው የክብር እንግዳ ጠቅላይ ሚኒስትር በጉባኤው ንግግር እንደሚያደርጉ እና ይህም በአፍሪካዋ ኢትዮጵያ እና በኦስትሪያ መካከል ያለውን ግንኙነት በተሻለ መልኩ እንደሚያሳድገው ይጠበቃል።

ባለፈው ሳምንት በጀርመን በተካሔደው የጂ20 ‘ኮምፓክት ዊዝ አፍሪካ’ (CWA) በተሰኘው ለውጥ ተኮር በሆነው ጉባኤ ላይ የአፍሪካ ሀገራት እና የተለያዩ አጋሮች ንግግር አድርገዋል፡፡ በዚህ የትብብር መድረክ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የኢኮኖሚ ትብብር እና የግሉን ዘርፍ ማጠናከር በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በተካሔደው ውይይት ላይ ተሳትፈዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጎን ለጎን ከፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ጋር በኮምፓክት ዊዝ አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ተገናኝተው መወያየታቸውንም በማህበራዊ የትስስር ገፅ ተጠቁሟል። “የተጠናከረው ግንኙነታችን እና ዘርፈ ብዙ ትብብራችን በመተማመን እና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ እና ዘላቂ ልማት ላይ ያተኮረ ነው” ሲሉ ጠ/ሚ ዐቢይ (ዶ/ር) በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ላይ ጽፈዋል።

ከኦስትሪያ እና ከጀርመን በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሳውዲ አረቢያም አቅንተው ነበር። በዓለም ላይ ጠንካራ ኢኮኖሚ እየገነቡ ካሉ ሀገራት መካከል ተጠቃሽ መሆን የጀመረችው ሳዑዲ አረቢያ፤ የ”ሳዑዲ-አፍሪካ” የመሪዎች ጉባኤን ለመጀመሪያ ጊዜ አዘጋጅታለች።

እንደሌሎቹ ጉባኤዎች ሁሉ የ”ሳዑዲ-አፍሪካ” የመሪዎች ጉባኤም በአፍሪካ ሀገራት እና በሳዑዲ አረቢያ መንግሥት መካከል ያለውን ትብብር ለማሳደግ ያለመ መሆኑን የሳዑዲ አረቢያ መገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ጠቁመዋል። በሳዑዲ አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ከተሳተፉ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ፣ ኤርትራ፣ ኬንያ፣ ሩዋንዳ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን፣ ታንዛኒያ እና ሌሎችም ሀገሮች በመሪዎቻቸው አማካኝነት ታድመዋል።

የአረብ ኒውስ ልዑሉን ጠቅሶ እንደጠቆመው፤ ትብብርን፣ አጋርነትን እና የንግድ ግንኙነቶችን ለማዳበር ባላቸው ጉጉት የ”ሳዑዲ-አፍሪካ” የመሪዎች ጉባኤን እንዳዘጋጁ ተናግረዋል፡፡ ይህ ጉባኤ የንጉስ ሳልማን የልማት ተነሳሽነት በአፍሪካ መጀመሩን የሚያበስር መሆኑንም በአረብ ኒውስ ተጠቁሟል።

አረብ ኒውስ በዘገባው እንዳብራራው፤ የሳዑዲ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ፤ የፖለቲካ ቅንጅቶችን ለማጎልበት፣ ቀጣናዊ የጸጥታ ስጋቶችን ለመፍታት፣ በጥናት እና በሀገር ውስጥ አዳዲስ የኃይል መፍትሄዎችን ለመፍጠር እና የኢንቨስትመንት ትብብርን ለማጎልበት እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅምን ለማስተዋወቅ ያስቻለ እንደነበር ተነግሮለታል።



በጀርመን የጂ 20 የ‘ኮምፓክት ዊዝ አፍሪካ‘ ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት

የጉባኤው ቀዳሚ ትኩረት በሳዑዲ እና በአፍሪካ መካከል የፖለቲካ፣ የክልላዊ ደህንነት እና የኢኮኖሚ አጋርነት ዙሪያ ትብብር እና ቅንጅት ማጠናከር ነው የተባለ ሲሆን፤ የአህጉሪቱ ሀገራት በጉባኤው ሃሳባቸውን እና ፍላጎታቸውን በመሪዎቻቸው አማካኝነት አንፀባርቀዋል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በ”ሳውዲ አፍሪካ” የመሪዎች ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ በኢትዮጵያ እና በሳዑዲ መካከል ያለው ግንኙነት ታሪካዊ እና ሥር የሰደደ መሆኑን በማስታወስ፤ እንዲህ ዓይነት ጉባኤ እጅግ በሚያነቃቃ መልኩ ግንኙነትን ለማደስ ይረዳል፤ ግንኙነታችንን ማደስ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ሳዑዲ እና ኢትዮጵያ ግንኙነታቸውን ማደስ እንዳለባቸው ከማስታወስ ባሻገር፤ አፍሪካ እና ሳዑዲ ያላቸው ጂኦግራፊያዊ ተቀራራቢነትን በመጥቀስ፤ እነሳዑዲ ከእንግዳ ተቀባዩ የአፍሪካ ሕዝብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከምንጊዜውም በላይ አሁን ማሳደግ እና መቅረብ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

ይህ በልዩ ሁኔታ በሳዑዲ እና በአፍሪካ መካከል እየታደሰ ያለው ግንኙነት አፍሪካ ያላትን ዕምቅ አቅም ለማንፀባረቅ የሚረዳ መሆኑንም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡ የሳዑዲ እና የአፍሪካ ግንኙነት መጠናከር በአህጉራዊ ደረጃ ተቀባይነት ባገኘው የልማት ዕቅድ የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063፣ የተባበሩት መንግሥታት የዘላቂ ልማት ግቦች እና የሳዑዲ የ2030 ራዕይ እንዲሳካ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብለዋል።

እነዚህን ራዕዮች እውን ለማድረግ የሁለቱንም የኢኮኖሚ ዕድገት እድሎች በመጠቀም የሳዑዲ-አፍሪካ ትብብርን ማጠናከር እና በተለይም የፋይናንስ ልማት ትብብርን ማሳደግ እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ጠቁመዋል።

ከኢትዮጵያ ጋር ባላት ግንኙነት ሳዑዲ የታዳሽ ኃይል፣ ጤና እና የትምህርት ዘርፍ ላይ ድጋፍ ማድረጓን በማስታወስ፤ በቀጣይ በጋራ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ትስስርን በማጠናከር የኢኮኖሚ ግንኙነት ላይ ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አመላክተዋል፡፡

አህጉራዊ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥን በተመለከተ ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ ከኢትዮጵያ አምስቱ የፖሊሲ ዋልታዎች መካከል ግብርና ዋነኛ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በዓመት ሁለት ጊዜ እየተመረተ መሆኑን፤ ከ6 ሚሊዮን ሔክታር ያላነሰ መሬት በእርሻ እየለመ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡ ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ የከተማ ግብርናን በማበረታታት የጓሮ አትክልት እና የእንስሳት እርባታ ላይ ሰፋፊ ሥራዎች በመሥራት ላይ መሆናቸውንም ተናግረዋል፡፡

በግብርናው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ሀብት በመመደብ በኢትዮጵያ ቢሳተፉ አፍሪካን ከማሳደግ ባሻገር የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንደሚቻልም ጠቁመዋል፡፡ ጨምረውም ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታት አረንጓዴ ልማት ላይ በስፋት እየተንቀሳቀሰች እንደምትገኝ አብራርተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የኢትዮጵያ አረንጓዴ ልማት ስኬትን በተመለከተ በሰፊው የተናገሩ ሲሆን፤ የሳዑዲ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ተሳታፊዎች በተለይም የመካከለኛው ምስራቅ ተዋናዮች ትብብር እንዲያደርጉ ጠይቀዋል። እ.ኤ.አ. ከ2019 ጀምሮ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል፤ ከ25 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን በየዓመቱ በሚያንቀሳቅሰው ግዙፍ የደን ልማት መርሀ ግብር ተግባራዊ እርምጃዎችን እየወሰደች ነው ብለዋል። ሀገሪቱ 32 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን መትከሏንም ተናግረዋል።

እ.ኤ.አ. በ2026 መጨረሻ ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ልማት ሥራዋን በማጠናከር፤ በአጠቃላይ 50 ቢሊዮን ዛፎች ትተክላለች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህ ለአንድ ዓመት ሙሉ በ64 ሚሊዮን ቤንዚን የሚንቀሳቀሱ መኪኖችን ከመንገድ ከማስወገድ ጋር ሊመሳሰል የሚችል መሆኑን ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሳዑዲ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ጎን ለጎን ከሳዑዲ አረቢያ አልጋ ወራሽ መሀመድ ቢን ሳልማን ጋር የሁለቱን ሀገራት ሁለገብ ግንኙነት እና አጋርነት ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይም ተወያይተዋል። በተጨማሪ ከጂቡቲው ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ኦማር ጊሌ እና ከሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሀመድ ጋር በሁለትዮሽ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል።

የሳዑዲ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ የፖለቲካ ቅንጅቶችን ለማጎልበት፣ የአካባቢውን የጸጥታ ስጋቶች ለመቅረፍ እና በጥናት እና በአካባቢው አዳዲስ የኃይል መፍትሔዎችን በማጎልበት ኢኮኖሚያዊ ለውጥን ለማስተዋወቅ ያለመ እንደሆነ ተጠቁሟል።

የሳዑዲ የዜና አገልግሎት ዘገባ እንዳመለከተው፤ በሳዑዲ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ በኩል ሳዑዲ አረቢያ የአፍሪካ አህጉር ሀብቷን እና ውስጣዊ አቅሟን ለመጠቀም የሚያስችሏትን አዳዲስ መፍትሄዎችን ለማግኘት ዓለም አቀፍ ጥረቶችን ለማጠናከር ያስችላታል ብሏል፡፡ ይህም የሳዑዲ መንግሥት ኢንቨስትመንት እና የልማት ፕሮጀክቶች በአፍሪካ ሀገራት በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ለመተሳሰር እንደሚያግዝ ዘገባው አብራርቷል፡፡

ሳዑዲ አረቢያ በቀጣይም ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር፣ ወደ ሰፊ አድማስ ለማስፋት እና በተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ልማታዊ ዘርፎች ፍሬያማ አጋርነት ለመመስረት እንደምትፈልግ የሳዑዲ የዜና አገልግሎት ዘግቧል።

ይህ የመሪዎች ጉባኤ በክልላዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የመንግሥቱ አመራር ሚና እና በገንዘብ ሚኒስትር አህመድ ሺዴ የሚመራ ሌላኛው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በሪያድ በሳዑዲ አረቢያ-አፍሪካ ኢኮኖሚ ኮንፈረንስ ላይ መሳተፉን አስታውሶ፤ ከኮንፈረንሱ ጎን ለጎን ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሳዑዲ አረቢያ አቻቸው መሀመድ አል ጃዳን ጋር ተወያይተዋል። በውይይታቸው ወቅት ሁለቱም ሚኒስትሮች በኢትዮጵያ እየተካሄደ ባለው የኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ በልማት ሥራዎች እና የዕዳ ማሻሻያ ሥራዎች ላይ ተወያይተዋል።

በዚህ ጉዳይ የሳዑዲ ዓረቢያ የገንዘብ ሚኒስትር መሐመድ አል ጃዳን መንግሥታቸው በኢትዮጵያ እየተካሄደ ላለው የልማት እንቅስቃሴ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ እና ሳውዲ አረቢያ በፔትሮሊየም እና ኢነርጂ ዘርፎች በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል። የትብብር ስምምነቱን በገንዘብ ሚኒስትሩ አህመድ ሺዴ እና በሳዑዲ አረቢያ የኢነርጂ ሚኒስትር አብዱላዚዝ ቢን ሳልማን አል ሳዑድ መካከል ተካሂዷል።

ስምምነቱ በሪያድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ እንደተገለጸው፤ ሁለቱ ሀገራት በነዳጅ አቅርቦት፣ በኃይል ቴክኖሎጂ ሽግግር እና በኃይል ኢንቨስትመንት መስኮች በትብብር ለመስራት ያስችላል ተብሎለታል። የመግባቢያ ሰነዱ በኃይል መስክ የሚደረጉ የልማት ሥራዎችን እና የነዳጅ አቅርቦትን ለኢትዮጵያ ለማረጋገጥ እንደሚያበረታታ ተጠቁሟል።

የፖለቲካ ተንታኞች ሳውዲ አረቢያ ከምንጊዜውም በላይ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ጠንካራ የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን ግንኙነት ለመፍጠር በንቃት እየሰራች ነው ያሉ ሲሆን፤ ስብሰባው በሳይንስ፣ በትምህርት፣ በኢኮኖሚ፣ በባህልና በሌሎችም ቁልፍ ዘርፎች ትብብር እንደሚያሳድግ ጠቁመዋል።

ከመሪዎቹ ጉባዔ ጎን ለጎን የሁለቱም ወገኖች 25 ወጣት ልኡካን የሚወከሉበት የሳዑዲ-አፍሪካ ወጣቶች ፎረምም ተካሂዷል።ፎረሙም የአፍሪካ ወጣቶች ልዑካን በሳይንስ ዘርፍ ያላቸውን ዓለም አቀፍ ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ ያስችላል ተብሏል። ከጉባዔው ጋር ተያይዞ የሳዑዲ አልጋ ወራሽ መሀመድ ቢን ሳልማን በአፍሪካ የንጉስ ሳልማን የልማት ተነሳሽነት መጀመሩን እና በአህጉሪቱ በ10 ዓመታት ውስጥ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚሸፍኑ ልማታዊ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞችን ይፋ አድርገዋል።

ኢትዮጵያና ሳዑዲ አረቢያ በንግድ፣ በኢንቨስትመንትና በሌሎች ዘርፎች ጠንካራ ትብብር ያላቸው ሲሆን፤ የሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በ1948 የጀመረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ሳዑዲ አረቢያ ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ ከከፈቱ ከመጀመሪያዎቹ የአረብ ሀገራት ተርታ መመዝገቧን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ሳዑዲ በሰፊው ከአፍሪካም ሆነ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር ጥረት ያደረገች የዘመኑ የመጀመሪያዋ ሀገር አይደለችም፡፡ የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የ49 ሀገራት መሪዎች የተሳተፉበት ሁለተኛው የአሜሪካ- አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤም አሜሪካን አካሂዳለች። በቀጣይ ወር ታኅሳስ ላይ ይኸው የአሜሪካ- አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ለሦስተኛ ጊዜ ይካሔዳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በሁለተኛው የአሜሪካ- አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ዓለማችንን እየፈተኗት ያሉ ተግዳሮቶች የአየር ንብረት ቀውስ፣ መልካም አስተዳደር፣ የምግብ ዋስትና እና የዓለም ጤናን የሚጨምር ሲሆን፤ እንዲሁም የአሜሪካ-አፍሪካ የንግድ እና የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማጠናከር ላይ ያተኮረ እንደነበር ተዘግቧል።

ጉባዔው አፍሪካ ቁልፍ የጂኦፖለቲካል ተጫዋች እንደሆነች ዕውቅና በመስጠት ላይ የተመሠረተ እንደነበር የተጠቀሰ ሲሆን፤ በመድረኩ ላይ አህጉሪቱ የአፍሪካን ህዝቦች ብቻ ሳይሆን የዓለምን የወደፊት ሁኔታ የምትቀርፅ መሆኑም ተዘግቧል።

በአሜሪካ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ለአፍሪካ ከተሰጠው ዕውቅና ባሻገር፤ አፍሪካ በቡድን 20 ውስጥ የአፍሪካ ኅብረት ቋሚ ቦታ የሚያገኝበትን ሁኔታ በተመለከተ መክረው ሕብረቱን አባል አድርገዋል። በተጨማሪም የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ ከአፍሪካ ሀገራት መካከል ቋሚ አባል እንዲያካትት ተነጋግረዋል።

ይህ ሁሉ ሀገራት አፍሪካን ለመሳብ የሚያደርጉት ጥረት ሲሆን፤ በቀጣይም አሜሪካን ጨምሮ ሌሎችም ሀገሮች ጉባኤ በማዘጋጀት እና ከሀገራቱ መሪዎች ጋር በመወያየት፣ በትብብር በመስራት ግንኙነታቸውን ይበልጥ እንደሚያጠናክሩ ይጠበቃል፡፡

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በፋሽን ኢንዱስትሪው ፈር ቀዳጇ አካል ጉዳተኛ

**አስመረት ብስራት**



ሳቤላ ከድር ትባላለች። የተወለደችው ኤርትራ አስመራ ከተማ ውስጥ ሲሆን በሁለት አመቷ ወደ አዲስ አበባ ለህክምና መጣች። ሳቤላ የተወለደችውም ሆነ ያደገችው ከአካል ጉዳት ጋር ነው። የአካል ጉዳቷ የተከሰተው እናቷ የዘጠኝ ወር ድረስ እርጉዝ እያለች አስመራ ውስጥ ድንገት ከጀርባዋ የሆነ ሰው ነክቷት ስትዞር መለመሉን ከቆመ የአእምሮ ህመምተኛ ጋር ተፋጠጠች። ልታመልጥ ስትሞክር ከፊት የነበረው ትልቅ ትቦ ላይ በፊቷ ወደቀች። በሰአቱ ሰው ተረባርቦ እናቷን ወደ ሆስፒታል ቢወስዷትም በጣም ብዙ ደም ፈሷት ስለነበር በሆዷ ያለችው ሳቤላ ከአካል ጉዳት ጋር እንድትወለድ ሆነ ።

በመካከል ዶክተሮቹ ፅንሱም የሳቤላ እናትም በጣም ከፉኛ እንደ ተጎዱ ለአባቷ እና ለቀሩት ቤተሰቦቻቸው የተናገሩ ቢሆንም ፅንሱ ምንም ቢሆን መትረፍ እንዳለበት ነገሯቸው ሳቤላ በኦፐራሲዬን ተወለደች። ስትወለድም በከባደ ሁኔታ የተጎዳች ህፃን ሆነች።

ከህፃንነት ጊዜዋ ጀምሮ ለበርካታ ጊዜ ትልልቅ ቀዶ ህክምናዎች ማድረጓን የምትናገረው ሳቤላ ስትወለድ አይኗ እጇና እግሯ ብቻ ጉዳት የነበረበት ሲሆን እስከ አስራ አንድ አመቷ ድረስ መንቀሳቀስ ምግብ መብላትና ሌሎችን ነገሮች በቤተሰብ እርዳታ ነበር የምታደረርገው።

ከ11 አመቷ በኋላ በቀዶ ህክምናና በሌሎች የህክምና እርዳታዎች መንቀሳቀስ ጀመረች። ቀስ በቀስም መራመድ ጀመረች። ከአካል ጉዳቱ በላይ የአእምሮ ጉዳት ይኑርባት አይኖርባት ያልተረዱት ወላጆቿ አእምሮዋ ደና መሆኑን የሚያረጋግጠ ምርመራ ካደረጉ በኋላ በእዝልም ቢሆን ትምህርት ቤት እየወሰድን እናስተምራታለን በማለት የትምህርት አለምን አስተዋወቋት።

ቤተሰቦቿ ለእሷ ብለው ብዙ መሰዋእትነት ከፍለዋል ትምህርት ቤት ከጓደኞቿ የተለየች አካል ጉዳተኛ መሆኗ ለብዙዎች እንደ ትንግርት መታየት ከዛም አለፍ ሲል ህብረተሰቡ ለአካል ጉዳት ባለው ዝቅተኛ ግንዛቤ ከእርግማን ጋር በማያያዝ ቤተሰቦቿም የተለዩና የተገለሉ ሆነው እንደ ነበር ታስታውሳለች።

በአስራ አንድ አመቷ ትምህርት ቤት የገባችው ሳቤላ ሶስት አመታትን በተከታታይ ደብል በመምታት በፍጥነት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ቻለች። ልጇን ለማስተማር በየቀኑ እያዘለች ትምህርት ቤት የምታደርሰው እናት ልጇ ላይ የሚደርሰውን ጫና እንዳትሰማ ሳቤላ ዝም ማለት ጀመረች።

በትምህርቷ በጣም ጎበዝ መሆኗ እሷም ተማሪዎችን ለማቅረብ በመጣር ብዙ ጓደኞችን ለማፍራት ቻለች፤ ይህም በአካል ጉዳት ምክንያት የሚደደርስባትን አድሎና መገለል ለመቀነሰ አስችሎኛል ትላለች። ይህች ወጣት አካል ጉዳተኞች ስለጉዳታቸው እያሰቡ ከሰው ከመሸሽ ይልቅ ወደ ሰዎች ቀርበው አቅማቸውን ማሳየት እንደሚገባቸውም ታስረዳለች።

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷንም ከመጀመሪያው በተሻለ ሁኔታ ከተማሪዎች ጋር በመቀራረብ አስራ አንደኛ ክፍለ ስትደርስ እናትና አባቷ ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው በእግር መንቀሳቀስ ከበዳት።

በእግር በመሄዷ ምክንያት እግሯ ቆስሎ ለአመት ትምህርት አቋርጣ ህክምናዋን መከታተል ጀመረች። ከዛ በኋላ ጫማ ማድረግ ጀመረች። "እግሬ የተገለበጠ መሆኑ ጫማ ማድረግ ይከብደኛል ኢትዮጵያ ውስጥ አካል ጉዳተኞችን አስበው ቢሰሩ መልካም ነው " ትላለች።

"...ሰዎች ድንገት ሲመለከቱኝ ይደነግጣሉ መደንገጣቸው ቢያስከፋኝም መቀየር በማልችለው ነገር ከመጨነቅ ወደተሻለው መትጋት መርጫለሁ " የምትለው ሳቤላ " አሁን ያለኝ አካል ጉዳት የእግር የእጅ የአይንና የህብለሰረሰር (ስፓይናል ኮርድ) ጉዳት መሆኑ ህይወቴን ከባድ አድርጎብኛል" ትላለች።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ከጉዳቷ ጋር እየታገለች አጠናቃ ውጤት ብታመጣም ዝንባሌዋ ወደ ጥበብ (አርት)ላይ ነበርና" ሚራክል" የተባለ የፊልም ትምህርት ቤት በትወናና በፊልም ኤዲቲንግ በእስክሪፕት አጻጻፍ ትምህርት ጀመረች ። ትምህርት ቤቱ ፎቅ ላይ ስለነበር

**የፋሽን መድረኩን ለማዘጋጀት ያሰበችው ሰዎች እየተዝናኑ ስለ አካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነበር። "ቢሮ፣ገንዘብ ሳየኖረኝ ነው ሥራውን የሠራሁት**

አሳንሰር ( ሊፍት ) አለመስራት፤ አስክሪብት አንብቦ መስራት፤ በተገቢው መልኩ ትወናውን መስራት በጉዳቷ ምክንያት ይከብዳት እንደነበር ታስታውሳለች።

"ከስድስት አመታት በላይ ፊልም ለመስራት በጣም ለፍቻለሁ። ማህበረሰቡ ላይ የአካል ጉዳትን የሚመለከት መልእክት በተገቢው መንገድ ለማስተላለፍ የተለያዩ ጥናቶች በማድረግ ለመስራት ሞክሬያለሁ። አካል ጉዳተኞች ማርገዝ መውለድ አይችሉም በማለት "የሚታሰበውን ነገር ለማስቀየር እስክሪብት ብጨርስም ወጪውን የሚሸፍንልኝ ማግኘት አልቻልኩም" የምትለው ሳቤላ "የተለያዩ ፊልሞችን ፅፌ ከፕሮዲሰሮች ጋር በስልክ አዳምጠውኝ ግን ልፈራረም ስሄድ የአካል ጉዳቴን አይተው ያባርሩኛል። ልለምን ሳልል ልስራ በማለት አጠገባቸው ብመጣም ማንም ሰው ሊረዳኝ ባለመቻሉ ፊልም የመስራት ህልሜን አቁሜ ቆም ብዬ አሰብኩና ሌላ ስራ ለመሞከር ተነሳሁ" ትላለች።

በዚህም በፋሽኑ ዘርፍ ለመሰማራት በማቀድ በ 2009 ዓ.ም የራሷን የፋሽን ዝግጅት በማድረግ ህልሟ ላይ የሚያደርሳትን ጉዞ አንድ ብላ ጀመረች ። የፋሽን መድረኩን ለማዘጋጀት ያሰበችው ሰዎች እየተዝናኑ ስለ አካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነበር። "ቢሮ፣ገንዘብ ሳየኖረኝ ነው ሥራውን የሠራሁት። አንዳንድ ተቋማት ምግብና አዳራሽ እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ አደረጉልኝ በዘርፉ ላይ የሚንቀሳቀሱ የፋሽንና የስነ ጥበብ ትምህርት ቤቶችም ስራቸውን በማቅረብ እንዲሁም ሞዴሎችን በመስጠት ስራው የተሳካ እንዲሆን አደረጉልኝ እኔም የመጀመሪያውን ፋሽነ ሾው ስራዬን ለእይታ አበቃሁ "ትላለች።

ከፋሽን ሾው ትዕይንት በኋላም አዲስ ዘመን ጋዜጣን ጨምሮ ሌሎች የግልና የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ስራውን አይተው በማድነቅ ለህዝቡ እንዲደሰርስ ትልቅ ሚና መጫወታቸውን ገልጻ፤ የአሜሪካ ኤምባሲ አካል ጉዳተኞች ፋሽን ሾ ሊያዘጋጅ ሲያስብ የሚያቋት ሰዎች ስለእርሷ ተናግረው ሸራተን አዲስ ላይ 28 አካል ጉዳተኞች በርካታ ጉዳት አልባዎች በአስር ፋሽን ዲዛይነሮች የተካተቱበት ስራ መሰራቱን ትናገራለች።

11 ፋሽን ሾዎች ላይ ስራዎቿን ይዛ ለማቅረብ የቻለችው ሳቤላ በራስ የመንቀሳቀስ አቅም ኖሯት ፋሽን ላይ የሰራች የመጀመሪያዋ አካል ጉዳተኛ መሆኗን ተናግራለች።

ምንም ነገር ለማድረግ የሚወስነው የራስ ጥንካሬ ነው የሚትለው ሳቤላ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ "ያልታበሱ እንባዎች" በሚል ፊልም ከተሳተፈች በኋላ ለአካል ጉዳተኛ በፊልም ሥራ መሳተፍ ብዙ ፈተና እንዳለውና በመጀመሪያ የሠሩት ፊልም ላይ ልምምድ ሲያደርጉ፣ በታዳሚዎች ፊት ወድቀው በደም የተለወሱበትን ቀን የማትዘነጋው መሆኑን ትናገራለች።

ሳቤላ እንደሌሎች አካል ጉዳተኞች በደረሰባት የአካል ጉዳት ተማርካ መከሊቷን መቅበር አትፈልግም። ይልቁንም "የተመቻቸ መንገድ መፍጠር የሚቻለው ያልተመቸ መንገድ ላይ ሆኖ ነው" ትላለች ።

"እሾህን በእሾህ" እንዲሉ፣ በሳቤላ ግንዛቤ መፍትሔ የሚፈጠረው ችግር ሲገጥም ነው። በመሆኑም አንዴ የተከሰተን ጉዳት እያሰቡ አንገት ከማቀርቀር፣ ችግሩ ከምንም ሥራ እንደማያግድ ለራስ መንገር የስኬት ቁንጮ ነው ትላለች።

"መስራት የሚቻለው በታጣው ነገር ሳይሆን ባለው ነገር ነው። በታጣ ነገር ላይ ሙጭጭ ማለት ያለውንም ማጣት ነው" ሳቤላ ሁሌም ለውስጧ የምትነግረው ሀሳብ ነው። "አካል ጉዳተኛ ነኝ" ብሎ መደበቅ፣ መውጣት የሚችለውን ችሎታ በመደበቅ ሌላም ጉዳት መጨመር ነው በማለትም ትመክራለች።

‹‹ጉዳቴን እኔ ፈልጌ አላመጣሁት፤ ደግሞስ ያልተሰጠኝን ብቻ ለምን እመለከታለሁ! ካልተሰጠኝ ይልቅ የተሰጠኝ ይበዛል እኮ...›› በማለት ራሷን እንደምታበረታ ነው የምትናገረው።

ሳቤላ ሁሌም የፈለገችውን መሥራት እንደምትችል ታምናለች። ይህ በራስ መተማመኗ ከአካል ጉዳተኞች ለየት ያለች እንደሚያደርጋት ታምናለች። "እንደ ሌሎች የኔ ዓይነት ሰዎች ጎደሎ ነኝ የሚለው ሐሳብ ቢያሸንፈኝ፣ የደረሰብኝ የአካል ጉዳት ለልመና በቂ ነበር" የምትለው ሳቤላ፣ ይህን ችግር በማለፍ በፊልም ሥራ ላይ ለመሳተፍ በቅታለች።

"አሁን ላይ ሳቤላ ከወንድምና ከእህቷ ጋር ትኖራለች። አላገባችም አልወለደችም አምላክ ከፈቀደ ማግባትንም መውለደንም ታስባለች።

ሳቤላ " ሰዎች አካል ጉዳተኞች ቢጢያቸውን ብቻ የሚያገቡ ይመስላቸዋል ሲወልዱም አካል ጉዳተኛ የሚወልዱ ነበር የሚያደርጉት ፤ አሁን ላይ ይህ አይነቱ አስተሳሰብ ተቀይሯል፤ እኔም እዚህ በመድረሴ ደስተኛ ነኝ " ትላለች።

"በተለይ እኛ አካል ጉዳተኞች ሴትም እንሁን ወንድ ሁሉም ነገር የሚመጣው ጊዜውንና ሰአቱን ጠብቆ እንደሆነ ማመንና ይኖርብናል፤ ምክንያቱም እኛ መወሰን አንችልም፤ ልክ እንደማንኛውም ጉዳት አልባ ሰው ትዳር ላይ የፍቅር ግንኙነት ላይ አለመግባባት ሊያጋጥመን ይችላል ያ ማለት ግን ጉዳተኛ ስለሆንኩኝ ነው ብሎ ራሰን ከመውቀሰ አጋራችንን በእውቀትና በተሻለ አእምሮ በልጠን ያለንን ግንኙነት ማጥበቅ ያስፈልጋል። ለጓደኝነትም ይሁን ለትዳር ያሰበንና የጠየቀን እኛ በመረጠን ሰው ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ግምትና ቦታ እንዲሁም ትልቅ የክብር በር ስለተከፈተልን ነው ።" ትላለች።

"የኔ ጉዳት ከሌሎቹ ጉደተኞች ጓደኞቼ ጋር ሳወዳድረው እጅግ በጣም ከባድ ነው። ግን አንድም ቀን ጌታ ሆይ ትዳር እንዳታሳጣኝ ብዬ አዝኜም ጠይቄም አላውቅም። ምክንያቱም ፈጣሪ ለእኔ ያዘጋጀልኝን እንደሚሰጠኝ አምናለሁ ። የጉዳቴ መጠን በሰዎች አይን ሲታይ እጅግ ከባድ ቢመስልም እኔ ግን ጉዳቴን አምኜ ተቀብዬው ወድጄው እና ቀለል አድርጌ ነው የምኖረው፤ እኔ የተመረጥኩኝ ነኝ እንጂ ምራጭ አይደለሁም ብዬ ሁሌም ለራሴ እነግረዋለሁ ።የተመረጥሽ ስትሆኚ ትኩረትሽ ለውጥና ስራ ላይ ይሆናል። ምራጭ ስትሆኚ ደግሞ ተገፊና ሰው ጠባቂ ጥገኛ ትሆኚለሽ ። ስለዚህ ህይወት እጃችን ላይ ናት ምድር ሁሉንም ተቀብላ ታኖራለች የሰው ልጅ ደግሞ መርጦ ይቀበላል መርጦ ይተዋል ። ስለዚህ ቀና እና መልካሙን እያሰብንና እየሰራን እንለፍ የመጣነው የተሰጠንን አላማ እንድንፈፅም ነው " በማለት መልእክቷን አስተላልፋለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ኢትዮጵያ ታሪክና ትውስታዋን ጥላ ያላለፈችባቸው አቀበትና ቁልቁለቶች የሉም። እኚህ ሁሉ የኢትዮጵያ ታሪክና ትውስታዎች የአዲስ ዘመንም ናቸው፡፡ ዛሬ "አዲስ ዘመን ድሮ" እያለ የድሮውን ሀገርና ሕዝባችንን ያስታውሰናል። በመዲናችን አዲስ አበባ የመንግሥት ገንዘብ በነፃ ልስጣችሁ እያለ የመረጠውን ሰው ወደ ሕንፃዎቹ ይዞ የሚገባው ግለሰብ ለ11ኛ ጊዜ ችሎት ቆሟል። ብልጧ ውሻ 4 ኪሎ ሜትሮችን አቋርጣ የጌታዋን በጎች አርደው የበሉትን ሰዎች ባለቤቱን እየመራች ወስዳ እጅ ከፍንጅ አሲዛቸዋለች። ብላቴን ጌታ ወልደ ጎሩይ ሥላሴ ኢትዮጵያ በፋሽስት በተወረረችበት ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት አቤቱታዋን ባለመሰማቱ ተበሳጭተው እራሳቸውን አጠፉ፤የሚል ነገርም አለ፤ እውነት ይሆን? የጳውሎስ ኞኞ ደብዳቤዎች እንደተለመደው ይጠብቁናል።

### ገንዘብ ልስጣችሁ እያለ የሚገፋፋው ተያዘ ተባለ

"እኔ የመንግሥት ሠራተኛ ነኝ። መንግሥት ለድሆች ገንዘብ በነፃ ለሚሰጥበት ክፍል ዋና ጸሀፊ ነኝ" በማለት ከዚህ በፊት አሥር ጊዜ በማታለል ወንጀል ተከሶ የነበረው ዘውዱ አንዱዓለም ለ11ኛ ጊዜ ተይዟል።

ተከሳሹ ከአዲስ አበባ ከተማ በተለይም ከምድር ባቡር፤ ከአውቶቡስ መቆሚያና ከልዩ ልዩ የገጠር ሕዝብ መገኛ ሥፍራ እየተዘዋወረ ባላገሮችን "ገንዘብ በነፃ የሚሰጥበት መሥሪያ ቤት አለ" በማለት ከአንዱ ሕንፃ በራፍ ቆሞ ባላገሮችን የሚያታልል መሆኑ በፖሊስ ተደርሶበታል።

ዘውዱ የገጠር ባላገሮችን የሚያታልለው አለባበሱን አሳምሮ ከአንድ ከፍተኛ ሕንፃ በራፍ በመቆም "ይኸ የእኔ መሥሪያ ቤት ነው" በማለት ፎቅ ቤት ለሰዎቹ አሳይቶ "ገንዘብ ለመውሰድ የሚፈቀድለት ከኪሱ ምንም ገንዘብ የሌለውና ራቁቱን የሆነ ብቻ ነው" በማለት ባላገሮቹን ከኪሳቸው በርብሮ ገንዘብ ወስዶ፤ ልብሳቸውን አስወልቆ አስቀምጥላችኋለሁ፤ በማለት በስተጀርባ በር በኩል የሚጠፋ መሆኑን ባለፈው ክስ ተረጋግጧል።

ተከሳሹ በአሁኑ ለ11ኛ ጊዜ የቀረበበት ክስ፤ ከሐረር ጠቅላይ ግዛት የመጡትን አቶ ተገኔ የተባሉትን ሰው ከባቡር ጣቢያ፤ ከባቡር ሲወርዱ ጠብቆ "ገንዘብ ከመንግሥት አሰጥዎታለሁ" በማለት ከአንድ ከፍተኛ ሕንፃ በራፍ ላይ ወስዶ ቢሮዬ ነው በማለት ልብሳቸውን አስወልቆ ከኪሳቸው 14 ብር ወስዶ በቁምጣ ሱሪ ብቻ ጥሏቸው ሔደ።

…,,,,….

**(አዲስ ዘመን ጥር 20 ቀን 1965ዓ.ም)**

ውሻዋ የጌታዋን በጎች ሰርቀው ያረዱትን ሌቦች አስያዘች

አቶ መኮንን ደሞሴ የተባሉ አዛውንት ያሳደጓት አንዲት ውሻ፤ የጌታዋን ሁለት በጎች በሌሊት ሰርቀው ወስደው ያረዱትን ሌቦች መርታ አሳይታ የበጎቹ ቆዳና ትርፍራፊ ሥጋ ከጭንቅላታቸው ተያዘ።

ብልጧ ውሻ በጎቹ ተሰርቀው ከተወሰዱ በኋላ ከታረዱበት ሥፍራ አጥር ዘልላ ገብታ ለምልክት የበግ አንጀት ይዛ ከባለቤቱ ፊት ቀረበች። ባለቤቱም በጎቹን ፈልገው ሰልችቷቸው ከቤታቸው ተቀምጠው ነበር።

አቶ መኮንን የውሻቸውን ፈለግ በመከተል ከአንድ አጥር ግቢ ደርሰው ለመግባት ስጋት ስላደረባቸው ከአጥር ውጪ ቆሙ። ብልጧ ውሻ ለሁለተኛ ጊዜ በአጥር ሾልካ ገብታ ሌላ የበግ ሳንባ ይዛ መጥታ ለጌታዋ አሳየች። የበጎቹ ባለቤትም 4ኛ ፖሊስ ጣቢያ ሔደው በማመልከት ግቢው ሲፈተሽ ተሰርቀው የታረዱት በጎች ጭንቅላታቸውና ቆዳቸው ተገኝቷል።

…….

በውሻዋ ጠቋሚነት ከተያዙት ሰዎች ቤት ከሌሎች ሰዎች የተሰረቁ 7 ኩንታል ጤፍና ግምቱ 5 መቶ ብር የሆነ ንብረት ተገኝቷል። ውሻዋ መርታ ያሳየችበት ሥፍራ ከጌታዋ መኖሪያ ቤት 4 ኪሎ ሜትር ይርቃል። ቦታውም አዲስ አበባ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን አጠገብ መሆኑ ታውቋል።

**(አዲስ ዘመን ህዳር 4 ቀን 1965ዓ.ም)**

ጨዋ ተመልካች

"ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር" የሚል የአበው አነጋገር አለ። ይህን ያልኩት ከሜዳ ገብተው ቢታዩ የኳስ አቋቋም የማይችሉ ሁሉ ብሔራዊ ተጫወቾቻችን ኢንተርናሽናል የእግር ኳስ ግጥሚያ ባደረጉ ቁጥር ጥላ ቢስ ነቀፋቸው የብዙዎቹን ጨዋ ተምልካች ጆሮ ስላሰለቸ ነው።

…..

ተጫዋቾቹን እየጠሩ መዝለፍና እግሌ ይግባ፤እግሌ ይውጣ ማለቱ ከሞራል ውድቀት በቀር የሚያስገኝ ነገር የለም። ማስገባትና ማስወጣቱ ያሰልጣኝ ፈንታ ነው። ዛሬ በሚደረገው ጨዋታ ፌዴሬሽኑ የጠራን ከያለንበት ተጠራርተን እንድንነቅፍ አይደለም። ስለዚህ ሁላችንም ወደ ስታዲየም ስንመጣ ለድጋፍ እንጂ ለተቃውሞ ሰልፍ አለመሆኑን አስቀድመን እንወቅ።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 13 ቀን 1968ዓ.ም)**

ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ

አዘጋጅ ጳውሎስ ኞኞ

*የፍቅር በሽታ ይዞኝ መሞቴ ነውና እባክህን ስለወንድ ልጅ አምላክ መድኃኒት ያለው እንደሆን ንገረኝ።

ከበደ አበራ

-መድኃኒት የለውምና ትንሽ ጊዜ ማቅ።

*ሱሪ ተንተርሰው ሲተኙ ሕልም ያሳያል ይባላልና እውነት ነው?

-እኔስ ሞክሬው አላውቅም፤እስቲ አንተው ሞክረው።

**(አዲስ ዘመን ታህሳስ 3 ቀን 1965ዓ.ም)**

* የኢትዮጵያ ፓርላማ አሁን የጀመረውን የሴተኛ አዳሪዎች ጉዳይ ወደ መልካም ግብ አድርሶት ያንን የሚናፍቀኝን ትዳር አግኝቼው እረካ ይሆን?

-ምናልባት ይሆን ይሆናል፡፡

**(አዲስ ዘመን ጥቅምት 10 ቀን 1964ዓ.ም)**

*ደካማ ጎኔን ብቻ ፈልጎ የሚጨቀጭቀኝን ወዳጄ ወይንስ ጠላቴ ማን ልበለው?

-ገንቢዬ!

*ብላቴን ጌታ ወልደ ጎሩይ ሥላሴ ኢትዮጵያ በፋሽስት ተወራ በነበረችበት ጊዜ፤ የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር አቤቱታዋን ሰምቶ ትክክለኛ ፍርድ ባለመስጠቱ ተበሳጭተው ሕይወታቸውን በገዛ እጃቸው አጠፉ የሚሉት እውነት ነው?

ምህረት ከበደ

- እንዲህ አይነቱን ወሬ ገና ዛሬ መስማቴ ነው። እኔ የማውቀው ታመው ነው የሚባለውን ነው።

*ከመሪ ሁሉ የትኛውን መሪ ታደንቃለህ?

ከበደ(ከበደሌ)

-መኪና ስገዛ እነግርሃለሁ!

**(አዲስ ዘመን ታህሳስ 15 ቀን 1966ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ



## 38 በመቶ አውሮፓዊያን በቀን ሦስቴ እንደማይመገቡ ተገለጸ

### ስለምግባቸው የማይጨነቁት 15 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

38 በመቶ አውሮፓዊያን በቀን ሦስቴ ምግብ የመብላት አቅም እንደሌላቸው ተገለጸ፡፡

742 ሚሊዮን የህዝብ ብዛት ያለው አውሮፓ 104 ትሪሊዮን ሀብት በመያዝ ከሁሉም አህጉራት ሀብታሙ አህጉር በመባል ይታወቃል፡፡

የአውሮፓ ባሮሜትር ይፋ ባደረገው ጥናት መሰረትም 38 በመቶ የአህጉሪቱ ህዝቦች በቀን ሦስት ጊዜ የመብላት አቅም እንደሌላቸው ገልጿል፡፡

በሁሉም የህብረቱ አባል ሀገራት ካሉ 10 ሺህ ዜጎች በዚህ ጥናት ላይ ተሳትፈዋል የተባለ ሲሆን በጥናቱ ከተሳተፉት ውስጥ 15 በመቶዎቹ ብቻ የኑሮ ውድነት እና የምግብ ዋጋ መናር እያሳሰበንም ብለዋል ሲል ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

እንደ ዘገባው ከሆነ በየዓመቱ እየናረ የመጣው የነዳጅ እና ምግብ ዋጋ ህይወታቸውን እየፈተነው ነው ያሉ ሲሆን በተለይም ችግሩ እየሰፋ የመጣው ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ነው፡፡

በጥናቱ መሰረትም 29 በመቶ አውሮፓውያን የገንዘብ አቅማቸው አደጋ ውስጥ ወድቋል የተባለ ሲሆን ከሁለቱ አውሮፓዊያን አንዱ በቀጣዮቹ ወራት ውስጥ ወደ ገንዘብ ቀውስ የመግባት አደጋ አንዣቦባቸዋልም ተብሏል፡፡

ከዚህ በፊት በተደረገ ጥናት 17 በመቶ አውሮፓዊያን የድህነት አደጋ ውስጥ ሲሆኑ ከ75 በመቶ በላይ አውሮፓዊያን ደግሞ በዋጋ መናር ምክንያት የገንዘብ አጠቃቀማቸውን ለማመጣጠን መገደዳቸውን ተናግረዋል፡፡

በብሪታንያ 6 ሚሊዮን ገደማ ዜጎች ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የተባለ ሲሆን፤ምግብ እና መሰል መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት እማይችሉበት ደረጃ ላይ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡

እነዚህ በድህነት ውስጥ የሚኖሩ አውሮፓዊያን የምግብ ፍላጎቶቻቸውን ለመሸፈን ቅናሽ ያላቸው የምግብ ባንክ እና ሌሎች ማህበራትን እየፈለጉ ነውም ተብሏል፡፡

በአጠቃላይ በኑሮ ውድነቱ ምክንያት በቀን ሦስቴ እየተመገቡ ያሉት 42 በመቶ የአህጉሪቱ ነዋሪዎች ብቻ ናቸው የተባለ ሲሆን 21 በመቶዎቹ ደግሞ ልጆቻቸውን ለመመገብ ሲሉ ቢያንስ አንድ ጊዜ የግድ መመገብ እንደሚያቆሙ በጥናቱ ላይ ተጠቅሷል፡፡



## የአየር ንብረት ለውጥ ዓለምን ወደ "ረሃብ ቀውስ" እየገፋ ነው - የዓለም ምግብ ፕሮግራም

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአየር ንብረት ለውጥ ዓለምን ወደ "ረሃብ ቀውስ" እየገፋ ነው ሲል የዓለም ምግብ ፕሮግራም አሳሰበ።

ከሶስት ቀናት በኋላ በዱባይ የሚጀመረው የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤም (ኮፕ28) የአየር ንብረት ለውጥ ቀውስ በሰው ልጆች የምግብ ዋስትና ላይ እያሳደረ ያለው ተጽዕኖ በስፋት እንዲመከርበት ነው ድርጅቱ ያሳሰበው።

ጉባኤው በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ለረሃብ እየተጋለጡ ለሚገኙ ሰዎች የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያመላክታል ተብሎ ይጠበቃል።

በ2022 ብቻ 56 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሰዎች ለምግብ ዋስትና ችግር ተጋልጠዋል የሚለው የዓለም ምግብ ድርጅት፥ አብዛኞቹ ተጠቂ ሀገራት ግጭትና አለመረጋጋት ያደቀቃቸው መሆናቸውም ችግሩን ይበልጥ እንዳባባሰው ገልጿል።

የመንግሥታቱ ድርጅት በዱባይ በሚካሄደው የኮፕ28 ጉባኤ የእርሻ፣ ምግብ ዋስትና እና አየር ንብረት አለማቀፍ ማዕቀፍ ይፋ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።

በዓለም የእርሻ ድርጅት (ፋኦ) የሚመራው ይህ አዲስ አለማቀፍ ጥምረት በአረብ ኤምሬትስ ድጋፍ ይደረግለታል ተብሏል።

አለማቀፍ ጥምረቱ የአየር ንብረት ለውጥ በምግብ እና ግብርና ዘርፎች ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ የተለያዩ ሃሳቦችን እንደሚያቀርብ ይጠበቃል ሲል የዘገበው አል ዓይን ኒውስ ነው።

# “ድሮ” ላይ መቸከል የፖለቲካ ቆሞ ቀርነት ነው

በእምነት

ግዜ አንድ ቦታ ቆሞ አይጠብቀንም። የእኛም እድሜ እንዲሁ። ቀን አልፎ ቀን ሲተካ፤ ወራት ወራትን እየቀየሩ ዓመታት ሲቆጠሩ የተወለደው ያድጋል፤ ጎረምሳውም ይጎለምሳል፤ ጎልማሳውም ወደ እርጅናው ተጠግቶ፣ ያረጀውም እንደየጥሪው ወደማይቀረው ዓለም ይሄዳል። ይህ የተፈጥሮ ጠባይ የሕይወት ኡደትና ጥሬ ሀቅ ነው። ይህንን የተፈጥሮ ግዴታ “አልቀበልም አሻፈረኝ!” ብሎ በቆመበት የሚቀርም የለም፤ ሊኖርም አይችልም። የሚሞክር ቢኖር እንኳን ተፈጥሮ እራሷ ሳይወድ በግድ እጅ እንዲሰጥ ታስገድደዋለች።

በዚህ ኡደት ውስጥ እድሜ መቁጠር አልያም በአካል መግዘፍ ብቻ በቂ አይደለም። በአስተሳሰብም ላቅ ማለት ያሻል። ከእለት እለት የተሻሉ ነገሮችን እየጨመሩና እራስን እያሻሻሉ መሄድ ይገባል። ዛሬ ልጅ የነበረው ነገ በጊዜ ሂደት በአካልም በአእምሮም ያድጋል። ከፋ ደጉን ለይቶ ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለአገሩ ጠቃሚ ዜጋ ይሆናል።

ግዜ ለሁላችንም እኩል የተሰጠ ከተጠ ቀምንበት እንደ አመጣጡ ካስተናገድነውም ብዙ የምናተርፍበት ነው። በጊዜ ውስጥ ሰው ብቻውን አይቀየርም። ዘመንም እንዲሁ የራሱ እሳቤና ስልጣኔን ይይዛል። የወል እሳቤ “ፋሽን” ይመጣል። በዚህ ግዜ

“አይ እኔ ዘመኑን አልመስለም፤ አልከተ ልምም፤ የቀደመው ይሻለኛል” ካልን ለውጥን የምንቃወም የቀደመው እሳቤና የዘመን ላይ የተቸከልን ያደርገናል። ለዚህ ሁሉ አባባሌ መነሻ የሆነኝ ቁምነገር “እንደ አገርም ሆነ እንደ ማህበረሰብ አሁን ላይ ግዜ የደረሰበት ስፍራ ላይ ደርሰናል? ግዜ የሚጠብቅብን ንቃተ ህሊናስ አለን ?” የሚለው ጥያቄ በውስጤ ስለሚመላለስ ነው።

የ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ የፈጠራ ብሎም ከፍ ያለ የስልጣኔ ዘመን ነው። ይህ ሁሉም ጤነኛ አእምሮ ያለው ሊስማማበት የሚችል የወል እውነት ነው። ዓለም ተቀይራለች። መቀየር ብቻ ሳይሆን በዘመናዊ አስተሳሰብና ስልጣኔ ተሻሽላለች። ግራ አጋቢው እውነታ ግን በዚህ ዘመን ላይ እየኖሩ ትናንት ላይ ተቸንክረው መንቀሳቀስ ያልቻሉ ሰዎች የመኖራቸው ጉዳይ ነው። ይበልጥ የሚያሳስበው ደግሞ በእድሜ ገፍተው፤ በአካል ገዝፈው “ተምረዋል ተመራምረዋል” የሚለውን ማእረግ ደርበው በዚህ እውነት ውስጥ የመገኘታቸው ጉዳይ ነው።

በተለይ በዚህ ዘመን ያሉ አብዛኞቹ ኢትዮጵያዊ ፖለቲከኞቻችን የቆሙበትን/የሚኖሩበትን ዘመን የሚዋጅ ማንነት አላቸው? ዓለም በስልጣኔ፣ በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ፣ በኢኮኖሚ እንዲሁም በፖለቲካ የት እንደ ደረሰስ ያውቃሉ? ሚስጥሩንስ ተገንዝበዋል የሚለው ጥያቄ አብዝቶ በውስጤ ይመላለሳል።

ለአመክንዮው መሰረት የሆነኝ ዛሬም ድረስ የፖለቲካዊ ቅራኔያቸውን (ልዩነታቸውን) በሰላማዊ መንገድ በውይይት የመፍታት ፍላጎቱን በማጣታቸው ምክንያት ነው። ከዛ ይልቅ ፈጥነው ማኩረፍ፤ ወደ ግጭት የሚወስዱ መንገዶችን መምረጥ፣ አብዝቶ የሚታይባቸውና ዋነኛ የባህሪያቸው መገለጫ እንደሆነ በሙሉ ልብ መናገር እችላለሁ። በሁለተኛነት እነዚህ አካላት እንወክለዋለን ለሚሉት ሕዝብ ከልብ የመነጨ በጎ ሀሳብ ሳይሆን በስሙ መነገድ የሚፈልጉ መሆናቸው ከስሪታቸውና ባህሪያቸው መገንዘብ ይቻላል።

ግዜ ለሁላችንም እኩል የተሰጠ ከተጠ ቀምንበት እንደ አመጣጡ ካስተናገድነውም ብዙ የምናተርፍበት ነው። በጊዜ ውስጥ ሰው ብቻውን አይቀየርም። ዘመንም እንዲሁ የራሱ እሳቤና ስልጣኔን ይይዛል። የወል እሳቤ “ፋሽን” ይመጣል

ይህ ባህሪያቸው ዘመኑን የሚዋጅ ነው ብሎ ማሰብ የሚቻል አይመስለኝም።

የፖለቲካ ምሁራን “ፖለቲካ በስሜት ሳይሆን በስሌት የሚሰራ ነው” ይላሉ። እኔም በዚህ ሀሳብ እስማማለሁ። የሰው ሕይወት እያስያዙ ቁማር በመቆመር የሚገኝ ፖለቲካዊ ትርፍ የለም። በንጽሀን ተስፋና ደም ከመነገድ ባለፈ ትርጉም ያለው ፖለቲካዊ ትርጓሜ ሊሰጠው የሚችል አይደለም። መጨረሻውም የዜሮ ድምር ከመሆን አያልፍም።

ኢትዮጵያውያን እንደ አገር ብዙ ጦርነቶችና አለመረጋጋቶችን አሳልፈናል። ለዚህ ምክንያቱ እንደ ማሕበረሰብ ቁጭ ብለን በችግሮቻችን ዙሪዩ መወያየት አለመቻላችን ነው። ችግሩ ዛሬም ዘመንን ተሻግሮ ያለቀቀን ትልቁ በሽታችን ሆኖ ቀጥሏል። አሁንም በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን፣ በችግሮቻችን ላይ ተወያይተን፣ ቆምንለት የምንለውን ሕዝብ ደህንነት ከማስጠበቅ ይልቅ ነፍጥ አንግበን አገርን ማወከን ምርጫችን አድርገናል።

በተለይም በአገራችን ያሉ “ነጻ ያልወጡ ነጻ አውጪዎች” “ሰላም ይሻላል” ሲባሉ ጦርነት ምርጫቸው ያደረጉ ናቸው። እኔም እነዚህ አካላት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያልተገነዘቡ ከግዜው እሩቅ ወደኋላ የቀሩ ይመስሉኛል። ያለንበት ዘመን ይህንን የሚፈቅድ አይደለም። ግዜው ያመጣውን ዘመናዊ እድሎችን ሁሉ ተጠቅሞ ሰላምን ማስቀደም ከምንም በላይ ተጠቃሚ ያደርጋል።

የኢፌዴሪ መንግሥት ከአንድ ዓመት በፊት ከሕወሓት ጋር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ባደረገው የሰላም ስምምነት ለሁለት ዓመት የዘለቀው ጦርነት እልባት ማግኘቱ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። ከጦርነት ማንም አያተርፍም። በውይይትና በመነጋገር ሰላምን ማስቀደም ስልጡንነት ነው። በዚህ ምክንያት መንግስትም ሰላም ወዳድ ሆኖ ያቀረበው የእንስማማ ጥያቄ ብዙ ነገሮችን ቀይሯል። ከጠፋው የበለጠ ውድመት እንዳይከሰት ብልህ ውሳኔ ወስኗል።

ዛሬም ግን በተለያዩ አካባቢዎች ድሮ ላይ ቆመው አስተሳሰባቸውን ወደዛሬው ነባራዊ ሁኔታ ማምጣት የተሳናቸው የጦር ሰባቂዎች አሉ። ከአንዴም ሁለት ጊዜ ለድርድር ተጠርተው ነበር። ለድርድር ጠረጴዛ ላይ ቁጭ እንዲሉ ረጅም መንገድ መጓዝ ቢቻልም፤ የሚያቀርቡት ሃሳብ ውሃ ቢወቅጡት አይነት ሆኖባቸው እነሆ ሳይሳካ ቀርቷል።

ይህ በእውነቱ በጣም የሚያሳዝን ከማሳዘንም አልፎ የሚያሳፍር ተግባር ነው። በባህላችን “ተበደልኩ” ባይና “በደልህን አስረዳ፤ የበደለህም ይካስህ” ሲባል በደሉን አስረድቶ የሚፈለገውን በግልጽ ተናግሮ በዚያኛው ወገን ያለውም አለኝ የሚለውን ሃሳብ አቅርቦ፣ አሸማጋይም መካከል ሆኖ “ከናንተ ይቅር” በማለት የሚበጀውን ሲወስን አልቀበልም ማለት ነውር ነው። ይህ እንደውም የሚያሳየው ከመጀመሪያውም ተበዳዩ ይዞት የቀረበውን ሃሳብ አያምንበትም አልያም ምናባዊ ነበር ማለት ነው።

ይህም ቢሆን ግን ዛሬም በዚህ አለመግባባት ተጎጂዎቹ እኛው ነን። ነጻ አውጪውን ጨምሮ፤ አገራችን አንድ እርምጃ ወደፊት ሁለት እርምጃ ወደኋላ እየተጎተተች ዜጎቿ ለእልቂት ለመፈናቀልና ለስደት እየተዳረጉ በአሳር በመከራ የሚገኘው ሀብት እየባከነ ሕዝብ ሁሌም በድህነት አረንቋ ውስጥ እንዲዘፈቅ እየሆነ ነው። በመሆኑም ሁሉም ነጻ አውጪ ኃይል የቆመበትን ዘመን ታሳቢ በማድረግ የኋሊት መንፏቀቅን በመተው ወደፊት በሚያራምዱ ሃሳቦች ዙሪያ ማተኮሩ ውጤታማ ያደርጋል።

ይህ ካልሆነ ግን ሁሌም ዘመን ይቀየራል ሌሎች አለማትም ጥለውን ይነጉዳሉ እኛ ግን በጦርነት አረር እየተጠበስን በረሃብ አለንጋ እየተገረፍን ለመቀጠል እንገደዳለን። ይህ ደግሞ ነጻ አውጪውንም ሆነ ሌላውን አካል የሚጠቅም አይደለም። እንደ ሀገርም ብሄራዊ ክብራችንን እየሸረሸረው የበለጠ አንገት የሚያስደፋ ችግር ውስጥ የሚከተን ነው።

በመንግሥት በኩል “ሕገ መንግሥቱንና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለመቀበል ዝግጁ ከሆነ ከማንኛውም ኃይል ጋር በውይይት ችግሮችን ለመፍታት ያለማሰለስ ጥረት አደርጋለሁ” ባለው መሰረት ጥረቶችን አደርጎ እያሳየን ነው። ለምሳሌ ያህል በሆደ ሰፊነት በአገራችን በተገለጠ የሽብር ስራው ከሚታወቀው የሸኔ ሽብርተኛ ቡድን ጋር ያለውን አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ በድርድር ለመፍታት ረጅም ርቀት ሄዷል።

ወገን እንዴት ነው ነገሩ! ከዛሬ 60 ዓመታት በፊት የነበረን የኦሮሞና የሌሎች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥያቄዎችን ይዞ ዛሬ ላይ ጦር መማዘዝ ውጤታማ ያደርጋልን ? እኔ እንደሚገባኝ እነዚህ ጥያቄዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተመልሰዋል። ያልተመለሱም ካሉም የአንድ አገር ዜጎች ነንና “ቢዘገይም አይረፍድም” እንደሚባለው በሰላማዊ መንገድ እንዲመለሱ ማድረጉ የተሻለ አማራጭ ነው። በዚህ ዘመን አውዳሚ በሆነው ጦርነት ጥያቄ ለማስመለስ ጥረት ማድረግ ወደ አሮጌው ዘመን በፍቃደኝነት ከመመለስ ተለይቶ የሚታይ አይሆንም።

ከዛሬ 60 ዓመት በፊት የነበረ ታሪክ ወይም ጥያቄ እያመዘዙ ሕዝብን ሰላም ከመንሳት፣ በሕዝቦቻችን መካከል አለመተማመን ከመፍጠር፣ ዘመኑን በሚዋጅ የፖለቲካ አስተሳሰብና ስልጡን መንገድ፤ ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅ፣ የቀጣዩን ትውልድ ነገዎች ብሩህ የሚያደርጉ ተሻጋሪ አስተሳሰቦችን ይዘው መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። የሕዝባችንም ፍላጎት ከዚህ የተለየ አይደለም።


መንግስት አገር አማን ብሎ ከተሰደዳችሁበት ሰብስቦ አብረን እንስራ ማለቱ የሚያስመሰግነው ነው። አሁን ላይም ቢሆን “ችግራችሁ ምንድን ነው ኑ እንነጋገር” በገለልተኛ አካል እንሸማገል ማለቱ ኢትዮጵያዊ ጨዋነቱ ከመሆኑም በላይ ዘመንን ቀድሞ የተረዳ ዘመንን የዋጀ አካሄድ ነው። “ሰላም አያሻኝም ጥያቄዬን ሁሉ በጦር ታጅቤ ሕዝብ እያሰቃየሁ እፈጽማለሁ” ለሚሉ ወገኖች ትዕግስትም ልክ እንዳለው እንዲገነዘቡት ማድረግ ያስፈልጋል።

መንግስት በሀገሪቱ ሰላም ሰፍኖ ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ጸጋዎች ወደ ሀብትና አቅም ቀይራ ብልጽግናዋን ታረጋግጥ ዘንድ ካለው ጉጉት በመነጨ ከግማሽ መንገድ በላይ ተጉዞ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ሞክሮ አልተሳካም። በመሆኑም “ምከረው ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው” ነውና ብሂሉ አሁን እንደ ሕዝብ የመንግስትን ቆራጥ እርምጃ ማየት የሚያሻን ወቅት ላይ እንደምንገኝ አምናለሁ።

ከቁርጠኝነትም ባሻገር የዜጎችን ሰላምና ደህንነት የማስከበር ኃላፊነቱን ከምን ጊዜውም በላይ የሚወጣበት ወሳኝ ምዕራፍም ነው። በመሆኑም መንግስት ስለትዕግስቱና ስለሰጠው እድል ሁሉ እንደ ሕዝብ ክብር እየሰጠን በቀጣይ ግን “ሰላማችን ይረጋገጥ፤ ወጥቶ የመግባትና በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ተንቀሳቅሶና ሰርቶ የመኖር መብታችን ይከበር ዘንድ ኃላፊነቱን ይወጣልን” ስንል ጥያቄያችንን እናቀርባለን።

አበቃሁ!

# ስፖርት



## ግልፅ ያልሆነው የፓሪስ ኦሊምፒክ ቅድመ ዝግጅት

ብርሃን ፈይሳ

የፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ ቅድመ ዝግጅትን በሚመለከት የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴርን ያገለለ ሥራ እያከናወነ መሆኑ ተጠቁሟል። የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ በበኩሉ መንግሥት ያላወቀውን ሥራ እያከናወነ አለመሆኑን ገልጿል።

ፈረንሳይ በታሪኳ ለሦስተኛ ጊዜ የምታዘጋጀው የ2024ቱ ኦሊምፒክ ሊካሄድ ወራት ብቻ እንደሚቀሩት ይታወቃል። ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ከዓመት አስቀድሞ የተለያዩ ዝግጅቶች መጀመሩን እንዲሁም በአውሮፓ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በማሰባሰብ ረገድ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። ይሁን እንጂ ኮሚቴው እያከናወነ ያለውን ተግባር የኢትዮጵያን ስፖርት በበላይነት የሚመራው የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እንደማያውቀው ገልጿል። ሰሞኑን ለ27ኛ ጊዜ በመቀሌ በተካሄደው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት የመንግሥትን አቅጣጫ በገለፁበት ወቅት ‹‹የፓሪስ ኦሊምፒክን ቅድመ ዝግጅት በሚመለከት ኮሚቴው እቅዱን እንዲያቀርብ ቢጠየቅም በቂ ምላሽ ካለመስጠቱም በላይ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና ክልሎችን ብቻ ነጥሎ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን በማግለል ከአዲስ አበባ እስከ ፓሪስ የሚል እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል›› ብለዋል።

ይህም አካሄድ ተገቢነት የሌለውና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ኃላፊነትና ስልጣን ያላካተተ መንግሥትም በመጨረሻ ‹‹ሀብት አምጣና ውድድሩ ላይ እንካፈል›› ቢባል መልስ ሊሰጥበት የማይችለው አስቸጋሪ ሁኔታ



የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣

ላይ መሆኑን አስገንዝበዋል። በዚህ ሁኔታ የሚዘልቅ ከሆነም የ2024 ኦሊምፒክ እንደባለፈው ኦሊምፒክ ችግር ውስጥ ሊጥል እንደሚችል ስጋታቸውን ገልፀዋል። ኦሊምፒክ የሀገራት የሰንደቅ ዓላማ እና ተሳትፎ ጉዳይ በመሆኑ የትኞቹም ሀገራት በብሄራዊ ደረጃ በማቀድና በመመካከር ይሰራሉ። ይህ ካልሆነ ግን በ2020 ኦሊምፒክ ያጋጠመው ችግር እንዳይደገም የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴም ሆነ አብረውት እየሰሩ የሚገኙት አካላት ከወዲሁ በጉዳዩ ላይ ግልጽ አቅጣጫ ይዘው እንዲሄዱ አሳስበዋል። ከእዚህ ውጪ የሆኑ አካሄዶች ግን በየትኛውም መንገድ ተቀባይነት የሌላቸውና መንግሥት ያስቀመጠውን ፖሊሲ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ያገለለ ሥራ ተቀባይነት እንደማይኖረው ተናግረዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ



የኦሊምፒክ ኮሚቴ ተወካይ አቶ ገዛኸኝ ወልዴ፣

ኮሚቴ ተወካይ አቶ ገዛኸኝ ወልዴ፣ በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ለተነሳው ጉዳይ ምላሽ ሰጥተዋል። በዚህም ኮሚቴው መንግሥትን ያገለለ ሥራ አለማከናወኑን የጠቀሱት ተወካዩ፤ ኮሚቴው የቅድመ ዝግጅት ሥራውን እያከናወነ ያለው ከመንግሥት ጋር መሆኑን ገልጸዋል። በ2024 ኦሊምፒክ መንግሥትም ሆነ ህዝቡ ትልቅ ነገር የሚጠብቅ እንደመሆኑ የኮሚቴውን እንቅስቃሴ መንግሥት እየደገፈው እንደሚገኝ አስረድተዋል። ‹‹የፓሪስ 2024 ኦሊምፒክን በሚመለከት ከፈረንሳይ ኤምባሲ ጋር ስንነጋገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሳያውቅ አልሰራንም›› ያሉት አቶ ገዛኸኝ፣ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋርም በመነጋገር እየተሰራ መሆኑንና ከዚህ ባለፈ የሚከሰቱ ችግሮችን ግን በውይይትና በመነጋገር መፍታት አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል። “ህዝቡን ተስፋ የሚያስቆርጥ ንግግር አስፈላጊ አይደለም “ ሲሉ አቶ ገዛኸኝ አክለዋል።

የኦሊምፒክ ቅድመ ዝግጅቱን አስመልክቶም የኮሚቴውና የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈጻሚዎች ከወራት በፊት ተገናኝተው ባደረጉት ውይይት ስራቸውን መጀመራቸውን ጠቅሰዋል። በዚህም መሰረት በ2020 ኦሊምፒክ የተፈጠሩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል እቅድ በማውጣት ከአምና ጀምሮ እየሰራ ሲሆን፤ በተለይም በአውሮፓ የሚገኙ በርካታ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በማነቃነቅ በገንዘብም ሆነ በሞራል እገዛ በማድረግ ውጤት ማምጣትና ሀገርን ማስጠራት ላይ ያተኮረ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል። በፓሪስ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ውይይት ከተደረገም በኋላ በተደረገው እንቅስቃሴ ከፓሪስ ወጣ ብሎ በሚገኝ ከተማ ኦሊምፒኩ ሊካሄድ ጥቂት ወራት ሲቀሩ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሄራዊ ቡድን ዝግጅት ሊያደርግ የሚችልበትን ሁኔታ በማመቻቸት ስምምነት ላይ መደረሱን ጠቁመዋል። በዚህም መሰረት ቡድኑ 42 ኪሎ ሜትር የሚሆን ርቀት ነጻ የመለማመጃ ጎዳና እንዲሁም ዘመናዊ የስልጠና አካዳሚ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል ብለዋል። ይህም የኢትዮጵያን በጎ ገጽታ ለመገንባት የሚደረግ ጥረት እንደሆነ ነው ተወካዩ ያስረዱት።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም ከ2020 የቶኪዮ ኦሊምፒክ በኋላ አመርቂ ውጤት ቢያስመዘግብም ህዝቡ ከሚጠብቀው ውጤት አንጻር ማሳካት ያልቻለው በምን ምክንያት ነው ሚለውን መገምገም፣ የአመራሩ የእርስ በእርስ ግንኙነት ምን እንደሚመስል እንዲሁም ከተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት ሰላማዊና ተቋማዊ መሆኑን በግልጽ እንዲመለከትና ለኦሊምፒኩ ከወዲሁ ዝግጅት እንዲያደርግ ሚኒስትር ዴኤታው አሳስበዋል።

ከገጽ 41 የዞረ

በመሆኑም ከዚህ በታች የተመለከተውን መመዘኛ መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ተጫራች በሀራጅ ሽያጩ ላይ መጫረት ይችላል።

1. የሚፈለገውን መመዘኛ መስፈርት አሟልቶ በሐራጅ ሽያጭ ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች ይህ የግልፅ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15/አሥራ አምስት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በሂደቱ መሳተፍ የሚችል ሲሆን የሀራጅ ጨረታው በ15ኛው ቀን የሚከናወን ይሆናል።
2. በሐራጅ ሽያጭ ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያለው፣ የዘመኑን ግብር የከፈለ ለመሆኑ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የምስክር ወረቀት እንዲሁም የግብር መለያ ቁጥር የሚያቀርብ መሆን አለበት።
3. የግልፅ የሐራጅ የሽያጭ ጨረታው በድርጅታችን ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት ይካሄዳል።
4. የሐራጅ ጨረታው በተቀመጠለት ሰዓት ውስጥ ካልተጠናቀቀ ላልተወሰነ ጊዜ ሊራዘም ይችላል።
5. የሐራጅ ጨረታ ሽያጭ የሚሳተፉ ተጫራቾች ጨረታው ከመጀመሩ በፊት ተመዝግበው ለሚወዳደሩበት ማለትም
   5.1. በ Bill Number ከ 1 እስከ 27 የቀረቡ DARK BLUE PREFORM WITH CAPS በጥቅል፣
   5.2. በ Bill Number ከ 1 እስከ 17 የቀረቡትን DIFFERENT SIZE OF GS PIPES በጥቅል፣
   5.3. በ Bill Number ከ1 እስከ 4 የቀረቡትን DIFEERENT TYPES OF GYPSUM MATERIALS በጥቅል፣
   5.4. በ Bill Number ከ1 እስከ 2 የቀረቡትን KOTA STONES, GI PIPES, IRON MOULDS, SELF ADHESIVE TAPES BUILDING MATERIALS, HARDWARE በጥቅል፣
   5.5. Bill Number 1 የቀረቡትን ASSORTED HOUSE HOLD ITEMS ስር ለተዘረዘሩት የተለያዩ ዓይነት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በC.P.O ከላይ በሰንጠረዥ1 ላይ በተመለከተው የጨረታ ጥቅል መነሻ ዋጋ መሰረት ተጫራቹ ለመወዳደር አሰርቶ መቅረብ ያለበት የመነሻ ዋጋውን 20% (ሃያ በመቶ) በEthiopian Shipping and Logistics Service Enterprise ስም ማሰራትና ማስያዝ የሚኖርበት ሲሆን የሚያሰሩት C.P.O በጥቅል መሆን ይኖርበታል፤ (በተናጠል C.P.O ማሰራት እና መወዳደር አይቻልም)።
6. የጨረታው አሸናፊ የሚለየው የጨረታ ሂደቱ በግልፅ ከተከፈተ በኋላ ውጤቱ ለድርጅቱ የበላይ አመራር ቀርቦ ውሳኔ ከተሰጠ እንዲሁም የአሸናፊው ውጤት በድርጅቱ ማስታወቂያ ቦርድ ላይ ለ3 ተከታታይ የሥራ ቀናት ከተለጠፈና ቅሬታ ካለ ቀርቦ ከተፈታ በኋላ ለአሸናፊው አሸናፊነቱን የሚገልፅ ደብዳቤ (Award Letter) እንዲደርሰው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።
7. የጨረታው አሸናፊ የሚለየው በሚሰጠው ከፍተኛ ዋጋ ይሆናል።
8. ከጨረታ መነሻ ዋጋ በታች ወይም እኩል መነሻ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች ከጨረታው ይሰረዛል፣
9. በሀራጅ ጨረታው የተሸነፉ ተጫራቾች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ CPO የጨረታው ውጤት በድርጅቱ የማስታወቂያ ቦርድ ላይ ለሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ተለጥፎ ከቆየ እና ቅሬታ ካለ ቀርቦ ከተፈታ በኋላ ተመላሽ የሚደረግ ሲሆን አሸናፊ ለሆኑ ተጫራቾች ከቀሪ ክፍያ ጋር ተዳምሮ የሚታሰብ ይሆናል።
10. በጨረታ ውጤቱ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ውጤቱ በጊዜያዊነት ይፋ በሚደረግበት ዕለት እንዲሁም ውጤቱ በድርጅቱ ማስታወቂያ ቦርድ ላይ ከተለጠፈበት ዕለት ጀምሮ ባሉት 3/ሦስት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በፅሁፍ ወይም በቃል ማቅረብ ይችላል፣
11. በአንድ ዝርዝር ውስጥ ተካተው ወይም በነጠላ ለሀራጅ ሽያጭ ለቀረቡ ንብረቶች ጨረታ ከ3/ሦስት/ በታች ተጫራች ከቀረበበት ኮሚቴው ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ውሳኔ ሲያገኝ ተፈፃሚ ይሆናል፣
12. የጨረታው አሸናፊ ማሸነፉ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ10 /አስር/ የስራ ቀናት ውስጥ ያሸነፈበትን ዕቃ ዋጋ ለድርጅቱ ገቢ ማድረግ አለበት። የጨረታው አሸናፊ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢ ካላደረገ ለጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ገንዘብ ለድርጅቱ ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል።
13. አሸናፊው ግለሰብ ወይም ድርጅት ያሸነፈበትን ገንዘብ ገቢ ባደረገ በ10/አስር/ የስራ ቀናት ውስጥ እቃውን መረከብ አለበት።
14. በጨረታው የተሸጠ እቃ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካልተነሳ የመጋዘን ኪራይ አከፋፈል የሚተመነው በደረቅ ወደብ አገልግሎት ታሪፍ መሰረት ሆኖ እቃው ከተሸጠበት ከ11ኛው ቀን ጀምሮ የገዛው ሰው እስከሚረከበው ድረስ የቆየበት ጊዜ ይሆናል።
15. ማንኛውም ተጫራች መጫረት የሚችለው በጥቅል የተመለከቱትን ሁሉንም የዕቃ አይነቶች አንድ ላይ ሲሆን ነጥሎ መወዳደር አይችልም።
16. በግልፅ የሐራጅ የጨረታ ሂደት አሸናፊ የሆነው ድርጅት አሸናፊ ለሆነበት ንብረት የሚጠበቅበትን ክፍያ ፈፅሞ ሲቀርብ ከሻጭ ድርጅት ጋር የገዥና ሻጭ ውል የመዋዋል ግዴታ ያለበት ሲሆን ንብረቶቹንም በናሙና እይታ ወቅት ባይውና ተስማምቶ ዋጋ ባቀረበውና አሸናፊ በሆነበት ሁኔታ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ንብረቶቹን ባሉበት ሁኔታ የመረከብ ግዴታ አለበት።
17. የናሙና እይታ፣ የC.P.O ማስገቢያ እና የሐራጅ ሽያጭ መርሀ ግብር ከስር በተገለፀው መሰረት መሆኑን እንገልጻለን።

| የዕቃው ዓይነት | የናሙና ዕይታ እና C.P.O ማስገቢያ ቀንና ሰዓት | የሐራጅ ጨረታው የሚካሄድበት ቀን እና ሰዓት |
|---|---|---|
| Dark Blue Preform with caps, Different size GS Pipes, Different types of Gypsum material, Kota Stones GI Pipes Iron Moulds Self, Assorted household items | • ታህሳስ 08፤09፣እና 10/2016 ዓ.ም<br>• ጠዋት ከ3፡00-6፡00 ሰዓት<br>• ከሰዓት ከ8፡00- 11፡00 ሰዓት | • የጨረታው ቀን ታህሳስ 12/2016 ዓ.ም ሲሆን<br>• ጨረታው የሚጀመርበት ሰዓት<br>• ጠዋት ከ3፡00-5፡30 ሰዓት<br>• ከሰዓት ከ8፡00-12፡00 ሰዓት |
| ማሳሰቢያ፡- የናሙና ዕይታ እና C.P.O ማስገቢያ ከላይ በተገለፀው ቀን እና ሰዓት ብቻ የምናስተናግድ መሆኑን እናሳስባለን፡፡ | | |

18. ድርጅቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 011-5-54 92 57/ 011-5-54 94 78 በመደወል ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይቻላል።

የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጆስቲክስ አገልግሎት ድርጅት